

አስኪ እንደገበያው መርህ እንነጋገር

ሐሳቡን የገለፀልን (ዶ/ር)

4

«ቴዲ አፍሮ ታስሮ ነበር እንዴ?!»

የመረጃ ምንጩ ኢቲቪ ብቻ የሆነ አንድ ወዳጄ በድንጋጤ የተናገረው

10

Economist.com



2ቱ

የጠ/ሚኒስትር መለስ ገጸታዎች

5

# አውራምባ ታይምስ

ስመረጃ ቅርብ ይሁኑ

2ኛ ዓመት ቁጥር 77 ነሐሴ 12 ቀን 2001 ዋጋ 3.50



ልዩ ቃለ ምልልስ

“ ይቅርታ የሚያስጠይቀኝ ነገር የለም፣ ይቅርታም አልጠየቅኩም። በእሥር የሚፈታ ማንኛውም ታራሚ ከማረሚያ ቤት ሲወጣ ሊያሟላ የሚገባው መስፈርት አለ። የምትወጣው የህግ የበላይነትን፣ የወንጀል አስከፊነትን ተምሬያለሁ ብለህ ነው። ያን አድርጌ ወጥቻለሁ። እኔ ሰው አልገጨሁም፣ አልገደልኩም ነገር ግን የፍ/ቤት ውሳኔን አከብራለሁ። ውሳኔውን አክብሬም የእስር ጊዜዬን ጨርሼ ወጥቻለሁ። ወደ ይቅርታ የሚወስደኝ ምንም ምክንያት የለም።

ቴዲ አፍሮ ከአውራምባ ታይምስ ጋር ያካሄደውን ልዩ ቃለ-ምልልስ በገጽ 8 ይመልከቱ

# «[ቃሊቲን] ለእኔ እንዲስማማ አድርጌ ተጠቅሜበት ወጥቻለሁ»

ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ)

በውስጥ ገፅ

መለስ ስለጨ ባይናገርም፣ ፈጣን ምላሽ የሚሹ ወሳኝ ጥያቄዎች አሉ

የኦርዌልያን ዴሞክራሲ

የአንድነት የአዳማ ስብሰባ በተቃውሞ ተቋረጠ

ኤዲቶርያል

# መልስ ሰጪ ባይኖርም፤ ፈጣን ምላሽ የሚሹ ወሳኝ ጥያቄዎች አሉ

አገር መልክዓ-ምድራዊ ወሰን፣ ተፈጥሮአዊ ክብሩና ነፃነቱ የተጠበቀ ሕዝብ፣ በሕግና በሥርዓት ዜጎቹን የመምራት ኃላፊነቱን የሚወጣ መንግስት ያለው ማለት ሲሆን በተጨማሪም፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊ፣ ባሕላዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች የሚካሄዱበት ሥርዓት የሰፈነበት ማለትም ነው:: ከዚህ ቀለል ያለ የትርጉም እሳቤ በመነሳት በሰፊ የታሪክ ሂደት ውስጥ ወደጐን የማይደረግ ሚና ያላት አገራችንስ የት ላይ ነች ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይመስለናል::

መልክዓ-ምድራዊ ወሰንን በተመለከተ፣ የዘመናዊ ስልጣኔ መሰረት በጣለችበት ሶስት ሺህ ዘመን ውስጥ የመልክዓ-ምድራዊ ወሰኗ የለየለት ምዕራፍ ኖሮት አያውቅም:: እስከ 20ኛው መቶ ክ/ዘመን መባቻ ድረስ በስፋት ይታመንበት የነበረው እጅግ የተለጠጠ ግዛት፣ ባለፉት መቶ አመታት ውስጥ በኢኮኖሚያዊ ፍላጐትና በፓለቲካዊ ጫናዎች ተሸራርፎ ከሞላ ጐደል አሁን ያለውን ቅርጽ እንዲይዝ ተገዷል:: እርግጥ፣ ከድንበር ጋር በተያያዘ በርካታ ያልተቋጩ ውዝግቦች አሉ:: ቢኖሩም፣ ኢትዮጵያዊያን አባቶች ሕይወታቸውን፣ አካላቸውንና ሀብታቸውን ገብረው፣ ኢትዮጵያችንን ከነዳር-ድንበሯ አስረክበውን አልፈዋል:: እኛስ ለቀጣዩ ትውልድ ምን አይነት ኢትዮጵያን ነው የምናስረክበው? የተከበረ ወሰን ያላት ሉአላዊት ኢትዮጵያን ወይስ በማይፈቱ ጥያቄዎች የታጨቀች አገር? ጉዳዩ የእያንዳንዱ ዜጋ ጉዳይ ነውና፣ ያለወሰን አገር የለምና፣ የባለድርሻነት ሚና ላላቸው ወገኖች በጠቅላላ ጥያቄዎቹን መሰንዘር ተገቢ ነው እንላለን:: በሌላ በኩል፣ የሕዝብ ተፈጥሯዊ ክብሩና ነጻነቱ ካልተጠበቀ፣ የዜጎች ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በፍትሃዊነት ካልተረጋገጠ፣ማሕበራዊና ባሕላዊ እሴቶች ጥበቃ ካልተደረገላቸው እና የሲቪልና ፖለቲካዊ እንቀስቃሴዎች ከተገደቡ በዘመናዊ ዓለማችን ሉአላዊ አገር አለ ለማለት አያስደፍርም:: እነዚህ ጉዳዮች እንዳይሟሉ እንቅፋት መሆን አገር እንዳትኖር አጥብቆ «ከመትጋት» አይተናነስም ብለን እናምናለን::

የአንድ አገር ዜጎች በአገሪቱ ውስጥ ያለውን ሀብት የመጋራትና እንደየችሎታቸው በየትኛውም የልማት ዘርፍ ያለምንም ፓለቲካዊ ጫና ለመሳተፍ የማይገረሰስ መብት አላቸው:: በግልጽ በተደነገገ ሕግ ክልከላ እስካልተደረገባቸው ድረስ በነፃ ምርጫቸው ምክንያት የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውን አያጡም ማለት ነው:: ይሁንና፣ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የመጨረሻ ዓመታት እየተደረገ ያለው የአባላት ምልመላ አላማና በመንግስታዊ መ/ቤቶች ውስጥ የሚደረገው ተመሳሳይ ጫና ግን ይህን መርህ በእጅጉ የሚጥስ በመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶት ተገቢው እርምት ሊደረግበት ይገባል እንላለን:: ሚሊዮኖችን በኢኮኖሚያዊ ጫና አባል ለማድረግ መሞከር ዜጎች አምራች እንዳይሆኑ

የመዳረግ አቅም አለው:: አህዝ ለማብዛት ደፋ ቀና ለሚሉትም የእንቧይ ካብ ከመካብ የዘለለ ፋይዳ የሌለው ጊዜን፣ ጉልበትና የአገር ሀብትን የሚያባክን መሆኑን ለማስታወስ እንወዳለን::

ለመሆኑ፣ አገሪቱ ትከተለዋለች በሚባለው የነፃ ገበያ ፓሊሲ ሽፋን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለው የኢኮኖሚ ብዝበዛ እንዴት ይታያል? የነፃ ገበያ ፓሊሲ መርህን ጥሶ በኢ-ፍትሃዊ መንገድ ትርፍ ለማጋበስና ማሕበራዊ ቀውስ የሚፈጥር የንግድ ሥርዓት እንዲፈጠር ያለከልካይ የሚተወኑትን መቆጣጠር የሚቻልበት ሕግ የታል? በጣም ጥቂት የስግበግብ ንግድ ተዋናዮች መላውን የአገሪቱን ሕዝብ የመኖር ህልውና የሚያናጋ መስመር ሲከተሉ በየትኛውም ዓለም እንደሚደረገው ሁሉ ሕግና ፖሊሲዎች የብዙሀኑን ጥቅም የሚያስከብሩበት ጥበቃ ለምን አይተገበርም? ሸቀጦች ከመደበኛ ዋጋቸው እስከ ሶስት በመቶ በየመደብሩ እየተቸበቸቡ ሕግ አለ ለማለት ይቻላል? የሸቀጦች ዋጋ በአስደንጋጭ ፍጥነት ሲያሻቅብ የኢኮኖሚው እድገት መገለጫ ነው ማለትስ ለ«ስግብግብ ነጋዴ» ተብዬዎቹ ስልታዊ ድጋፍ ማረጋገጫ አይሆንም? ሕዝብ እየተበዘበዘ ነው:: ፍትሃዊ ግብይት ይፈልጋል:: መንግስት ይህን የማረጋገጥ ኃላፊነት እንዳለበት ሊገነዘብ ይገባል:: ይህ ባለመሆኑ ሕዝቡ የመንግስትነት ተግባር ምን ሊሆን ነው? እያለ ይጠይቃል:: ጥያቄው ተገቢ ነው፤ ፈጣኝ ምላሽ ግን የለም:: እናም፣ ተገቢና ፈጣን ምላሽ ሊሰጠው ያሻል::

አብዛኞቹ መንግስታዊ መ/ቤቶችም ቢሆኑ ለሚቀርቡባቸው ሮሮዎች አፋጣኝና ተገቢ ምላሽ መስጠት ቢጠበቅባቸውም ተጠያቂነት የሌለባቸው የሚያስመስል ዘልማዳዊ አሰራር ላይ የሙጥኝ እንዳሉ ናቸው:: የመንግስት ተቋማዊ መዋቅሮች በአገር ላይ የሚያደርሱት አላፊ አግዳሚ የሚመለከተው ውድመትም አለ:: በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚመጡ የግብርና መሳሪያዎች፣ ማዳበሪያዎችና መድኃኒቶችን እንመልከት፤ በየዓመቱ ያለአግባብ በመከማቸታቸውና ዝውውራቸው ባለመጠናቀቁ ከጥቅም ውጭ የሚሆኑትን ተሽከርካሪዎች፣ ማሽነሪዎችና የግብርና ግብአቶችን አስመልክቶ ሪፖርት ይቀርባል:: ተግባሩ ይኮነናል:: የተጠየቀ አሰራሩ ዘልማዳዊና ደካማ ነው:: እንዴት? ለምን? ብሎ የሚጠይቅ የለም:: ቢኖርም ጠያቂው የጥፋቱ ጥልፍልፍ ድር ተባባሪ የሚሆንበትን መስመር በአዎንታዊ ሪፖርት ሽፋፍኖ እንዲያልፍ ይደረጋል:: የአገር ልማት ይደነቃቀፋል:: በዚህ መልኩ ዜጎች ዘላለማቸውን በድህነት እንዲኖሩ ይፈረድባቸዋል:: ከጥፋታችንና ካለፈው ስህተታችን ስንማር አንታይም:: ጥፋተኞች ለፍርድ ሲቀርቡ፣ «እንዳይደገም» በተግባር ሲተረጐም እምብኣም ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም::

መላ አገሪቷን የመታትን የሕገ-ወጥ ቤት ግንባታ ጉዳይም ሌላ አይነተኛ ምሳሌ ነው:: ቤቶች በሕገ-ወጥ መንገድ መገንባት ይጀምራሉ:: እንደእንጉዳይ ይፈላሉ:: የዜጎች ሀብት ይፈሳል:: ጊዜና ጉልበት ይባክናል:: ይህ ሁሉ ሲሆን በአገሪቷ ላይ የመንግስት ባለስልጣናት ሁኔታውን መመልከታቸው አይቀርም:: ይልቁንም ብዙዎቹ የተግባሩ ተሳታፊ በመሆን በሙስና ቅሌት የሚዘፈቁ ናቸው:: የሆነው ሁሉ ከሆነና ብዙ ሀብት ከፈሰሰ በኋላ «እርምጃ» ይወሰዳል:: አገር ማለት በነጻነት የሚኖሩ ዜጎች ናቸው::

ከፍተኛ ሀብት በሕገ-ወጥ መንገድ ሲፈስ የሚመለከታቸው ክፍሎች ዝም ሊሉ ባልተገባ። ይህን ሀብት ማፍረስ አገርን እንደማፍረስ ይቆጠራል። ዘግይቶ የሚገኝ ፍትህ ከነጭራሹ ፍትህን ካለማግኘት አይለይም። እርምጃዎች ሕጋዊነት የሚላበሱት በተገቢው ጊዜ ሲወሰዱ፣ የውሳኔነታቸው አንድምታ ሕግን የማስከበርና ማሕበረሰባዊ ተጠቃሚነትን ለማስፈን ሲሆን ብቻ ነው።

ከፍተኛ ሀብት ፈሶባቸው የሚገነቡ የመንገድ መከለያዎችና ሕይወት አድን የትራፊክ ምልክቶች፣ ጉዳት በሚደርስባቸው ወቅትም ተመሳሳይ ጥያቄ ይነሳል። አደጋውን ያደረሱት ወገኖች ተገቢውን ክፍያ ይከፍላሉ። እድሳት ግን የለም። መጀመሪያውኑ ሳያስፈልግ የተሰራ ያስመስላሉ። ይህም የአሰራር ዝርክርክነትና የተጠያቂነት አለመኖር ውጤት ነው። የሕዝብ ሀብት መሆኑን በመርሳት በሕዝብ አእምሮ ውስጥ ምንም አይነት ጥያቄ ቢፈጠር በግድየለሽነትና በዘልማዳዊ አሰራር የመቀጠል ተግባር ነው። እናም፣ ለሕዝብ ኢኮኖሚያዊና ሞራላዊ እሴቶች ዋጋ ይሰጥ እንላለን።

አገር አለ የሚባለው ተፈጥሯዊ ክብሩና ነፃነቱ የተጠበቀ ሕዝብ ሲኖር ነው ብለናል። ይህ የተለያዩ መገለጫዎች ቢኖሩትም የባሕላዊና ሞራላዊ እሴቶች መጠበቅ ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛሉ። መንግስት የማሕበረሰቡ የከበሩ የባሕል እሴቶች እንዲጠበቁ ኃላፊነቱን እየተወጣ ነውን? ብለን ስንጠይቅ ጥበቃና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ታሪካዊ ክፍሎች አደጋ ላይ መውደቃቸውን እንመለከታለን።

አንዱ የመቻቻል፣ ተከባብሮና ተፋቅሮ የመኖር ባሕላችን ነው። በኢትዮጵያ ረዥም የሕዝቦች አብሮ የመኖር ታሪክ ውዝግቦች ተፈጥረው አያውቁም፣ ግጭቶች አልነበሩም ልንል አንችልም። የተለያየ ባሕልና አኗኗር ባላቸው መካከል ብቻ ሳይሆን በአንድ ብሔር፣ እምነት ተከታዮችና በአንድ ጉጥ (መንደር) ውስጥ በሚኖሩ ዜጎች መካከል እንኳ ሰላማዊው የኑሮ ኡደት የሚደፈርስባቸው ጊዜያት አሉ። አሁን እየተከሰቱ ያሉ ግጭቶችና ውዝግቦች ግን የተለየ ባህሪ ያላቸው ናቸው።

አደጋውን ሊከላከሉ የሚገባቸው ባለአደራዎች በዚህ ተግባር ላይ መሰማራታቸው አሳፋሪና በብርቅዬ እሴቶቻችን ላይ የተቃጣ አደጋ ያደርገዋል። እነኚህ አይዞህ ባይ ያላቸው የአመጽ አራጋቢዎችም የእምነት ቅጥሮችን እየደፈሩ፣ ባሕላችንን መረጋገጫ እያደረጉት ነውና መንግስት ራሱን ሊፈትሽ፣ የአሰራር መዋቅሩን ሊመረምር ይገባል እንላለን። በየእምነት ተቋማቱ ጥጋጥግ እየተቸበቸቡ ያሉ የሌሎችን እምነት የሚያንቋሽሹ «የአትነሳም ወይ» የቅስቀሳ መድብሎችም ለምን በዝምታ እንደሚታዩ ግልጽ አይደለም። የእሴቶቻችን ጠንቆች ናቸው። ተከታትሎ ማስወገድና ተዋናዩቹንም ለፍርድ ማቅረብ ይገባል። ይህ ባለመሆኑ አሁንም ሕዝቡ የመንግስት ተግባር ምን ሊሆን ነው? እያለ ይጠይቃል። ተገቢና ፈጣን ምላሽ የሚሻ ጥያቄ ነው እናምናለን።

የሞራል እሴቶችም በአደገኛ ሁኔታ እየተጣሱ ይገኛሉ። ዜጎችን በተለይም ወጣቱን ትውልድ ለሥነ-ምግባር ዝቅጠት የሚዳርጉ የዝሙት አልበሞች እንደሕጋዊ ሸቀጥ በየጉዳናው እየተቸበቸቡ ነው። ልማዳዊ ድርጊት ሆኗል። አገራችን የአደንዛዥ-እጽ

ማዕከል እንድትሆን በሚሹ ግፌቶች ብዙዎችን እያጣን ነው። የሕፃናት ዝሙት አዳሪነትና የግብረ-ሰዶም ዝቅጠት እየሰፈነ ነው። በእርግጥም ኢትዮጵያችን እንደአገር የት ላይ ነች? ብለን አበክረን የምንጠይቅበት ጊዜ ላይ ነን።

እያንዳንዱን መንግስታዊ ተቋም መፈተሽ ብንጀምር ብዙ የሚባልላቸው የሥነ-ምግባር መርሆዎች ከቃል ያለፈ ዋጋ እንዳልተሰጣቸው ማረጋገጥ ይቻላል። የትውልድ አደራን በኃላፊነት ማስረከብም እንደቅንጦት የሚታይ አቋም ሆኗል። አብዛኞቹ፣ «ለመሆኑ የመንግስት ተግባር ምንድነው?» የሚል ተገቢ ጥያቄ የሚያጭሩ ናቸው። ጥያቄዎቹን የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ የመመለስ ታሪካዊ ኃላፊነትና ግዴታ እንዳለባቸው ሊገነዘብ ይገባል።

በመጨረሻ፣ መልክዓ-ምድራዊ ወሰኗ ፍትሀዊ በሆነ የሕግ አግባብ ተቋጭቶ ለቀጣዩ ትውልድ በኩራት የምናስረክባትን ኢትዮጵያን እንፈልጋለን። ክብራቸውና ነፃነታቸው የተጠበቀላቸው ዜጎች እንዲኖሩ በሕግና በሥርዓት የሚመራ፣ ተጠያቂነት የሰፈነበት መንግስት መዋቅር እውን እንዲሆን እንሻለን። ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊ፣ ባሕላዊ፣ ሞራላዊ እና የሲቪልና የፓለቲካ መብቶች ይከበሩ። ይህ ከሆነ፣ በእርግጥም ሁላችንንም የሚያስማማን የአገርነት እሳቤ እውን ይሆናል!!!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!

## መጣጥፎች

# ቡሄ ለልማት!

በአቤ ቶኪቻው
abeto2007@yahoo.com

## «ቴዲ አፍሮ ታስሮ ነበር እንዴ?!»

### የመረጃ ምንጩ ኢቲቪ ብቻ የሆነ አንድ ወዳጄ በድንጋጤ የተናገረው

ወዳጄ እንዴት ሰንብተዋል? ቡሄ በየደጃፋችን መጣ እንኳን አደረስዎ ማለት ይገባል። «ቡሄ ካለፈ የለም ክረምት» የሚሉት ነገር ካልቀረ «የደቀንነው ሳፋ» ሳይሞላ ክረምቱ ሊያልፍ ነው ማለት ነው። ጉድ እኮ ነው! ኤልፓዎች ቢያንስ ከቡሄ በኋላ እንኳን ፈረቃውን እንዲያስቀሩ የእኔ ሰፈር ልጆች አንድ ግጥም አዘጋጅተው ሰምቻለሁኝ። ልጆቹ ድሮ ድሮ ሆያ ሆዬ ብለው ሰሚ ሲጠፋ «አረ በቃበቃ ጉሮሮአችን ነቃ!» ሲባል የነበረውን ግጥም በማሻሻል «አረ በቃ በቃ መብራት በፈረቃ!» እያሉ ሲለማመዱ ነበር። እኔም

ይህንን ግጥም በሰማሁኝ ጊዜ ልማት ናፋቂ ነኝና፤ ቅን አሳቢ ነኝና ቡሄን ለልማት የሚል ሃሳብ በልቤ ተፀነሰ:: እነሆም ቡሄን እንዴት ለልማት? የሚለውን ዛሬ እናወጋለን::

**በቅድሚያ:-**

ብላቴናው ተፈቷልና እንኳን ደስ አልዎ ወዳጄ!

ከዚህ በፊት ቴዲ አፍሮ ሊፈታ እንደሚችል ጋዜጦች በዘገቡ ጊዜ እኔ ወገኛ ወዳጅዎም ወዳጆቼ ስለ ብላቴናው መፈታት ያሉትን፤ እኔም የተሰማኝን አንዳንድ ነጥቦች እያነሳሁ አውግቼዎ እንደነበር ያስታውሱ ይሆናል:: የዛን ጊዜ ከጠርጣሮች አንዷ የሆነች ወዳጄ አንድ የሙሽራ ታሪክ አውግታኛለች:: ታሪኩ ይህንን ይመስላል::

ሴትየዋ ባል መጣላት የአካባቢው ሰው የእንኳን ደስ አለሽ መልእክት ሲያስተላልፍላት «እንኳን አብሮ ደስ አለን!» ብላ ደስታዋን ገልፃ ሳታበቃ ባል ተብዬው እንዳይሆን ሆኖ ተመለሰ:: ደግነቱ አሁንም ሌላ ባል መጣ:: «እንኳን ደስ አለሽ!» ተባለች:: ተደስታ ሳታበቃ አሁንም ባልየው ሳይመጣ ቀረ... አሁን ሴቲቱ ለባል ያላት እምነት ስጋት ውስጥ ገባ:: ከዛ በኋላ «ባል መጣልሽ እንኳን ደስ አለሽ!» ሲሏት «ቆይ እስቲ ይምጣ እና ፈረሱ ላይ ልውጣ፣ እና ቤቱ ልግባ፣ እና ጫጉላ ይደረግ ከዛ በፊት አላምንም!» አለች:: («ቴዲ ሊፈታ ነው» ባልኩሽ ጊዜ ይህንን ተረት የተረትሽልኝ ወዳጄ አሁንስ አመንሽኝ?) ለማንኛ ውም ብላቴናው አሁን የእውነት ተፈቷል:: እናም እንኳን ደስ አላችሁ ብዬ ብል ቅር የሚለው አካል ያለ አይመስለኝም:: ይህንን ተከትሎ በሃገሪቱ የፍትህ ስርዓት መስፈኑንም እንደ ኢቲቪ ያሉ መገናኛ ብዙሃኖች ዘግበውታል:: (ፊደል በመግደፍ እንደ ኢቲቪ ያሉ መናኛ ብዙሃን ብላችሁ ያነበባችሁ ሰዎች ውርድ ከራሴ እኔ መገናኛ ብዙሃን ነው ያልኩት::) ይህ በእንዲህ እንዳለ:- የመረጃ ምንጩ ኢቲቪ ብቻ የሆነ አንድ ወዳጅ አለኝ:: ይህ ወዳጄን አንዳንድ ወዳጆቻችን «የኢቲቪ ዜና አንባቢው ራሱ እርሱ ቤት ዜና ሲያነብ እንደምን አመሸህ የሚለው በስሙ ጠርቶት ነው» እያሉ ያሙታል:: ታድያ ይህ ወዳጄ በቴሌቪዥን «አርቲስት ቴዲ አፍሮ ከእስር ተፈታ» የሚለውን ዜና በሰማ ጊዜ ጠላትዎ ክው ይበል ክው ብሎ ደነገጠ:: ሌሎች የደስታ ጩኸት ሲጮሁ የእርሱ መደንገጥ የደነቀው ሌላ ወዳጃችን «ምነው ደነገጥክ የገጨው አንተን ነበር እንዴ?» ሲል ቢጠይቀው ይህ ኢቲቪን ብቻ የመረጃ ምንጩ ያደረገ ወዳጄ ለወዳጃችን ማንጓጠጥ ቦታ ሳይሰጥ «ቴዲ አፍሮ ታስሮ ነበር እንዴ?» ሲል ጠየቀን:: በዚህ ጊዜ ሁላችንም ሳቅን:: ነገሩን ስንመረምር ግን የሚያስቅ ሳይሆን የሚያሳቅቅ ሆኖ አግኝተነዋል:: እንዴት? ይበሉኝ...

ወዳጃችን እንዳልኩዎ ወሬ የሚያገኘው ከኢቲቪ ብቻ ነው:: ታድያ ኢቲቪ አንድም ቀን የአርቲስቱን መታሰር ሲዘግብ ያልሰማው ወዳጃችን ዛሬ «ተፈታ» የሚለውን ዜና ሲሰማ «መቼ ታስሮ?» ቢል እንዴት ያስቃል? ያሳቅቃል እንጂ:: በእርግጥ ኢቲቪ በርካታ ልማታዊ ዘገባዎች እያሉት የአርቲስቱን እስር መዘገብ ከኢቲቪ ደረጃ ያወርደው ይሆናል ብለው የሚሉ ሰዎች እንዳሉ ይሰማኛል:: የሆነው ሆኖ ኢቲቪ የእስሩን ዘገባ

አልዘገበም (አሉ)፡፡  ስለዚህም ወዳጃችን ደነገጠ፡፡ ለምን? ቅድሚያ በቂ መረጃ ባለማግኘቱ... (ደሞ እንዲህ ብላችሁ ሃምሳ ብር ግብር ይበዛል በሉ አኳችሁ)

ከኢቲቪ ወሬ ሳንወጣ ባለፈው ሳምንት ውስጥ መኢአድ (መላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት) ባደረገው ህዝባዊ ስብሰባ በኢትዮጵያ ባንዲራ ላይ አንዳንድ የአቋም መግለጫዎችን አውጥቷል፡፡ ከነዚህ አንዳንድ መግለጫዎች ውስጥ በባንዲራው መሃከል ያለችውን ኮኮብ መኢአዶች እንሚቃወሟት ገልፀዋል፡፡ እነርሱ መግለጫውን በሰጡ በማግስቱ ታድያ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት «ባንዴራው ላይ ባለችው ኮኮብማ አትምጡብን» አይነት ይዘት ባለው መግለጫ መኢአድን ተቃውሟል፡፡ በበኩሌ ደስ ብሎኛል፡፡ እንዲህ ነው እንጂ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት! ስልም አድንቄያለሁኝ፡፡ ነገር ግን በኢቲቪ ሁልጊዜ እንዲህ አይነት ነገሮች ሲያጋጥሙ «ያወግዙ» የነበሩት አንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች የት ሔደው ነው የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ብቻውን ተቃውሞ የሚያሰማው? የኮኮቧ ነገር የአፋር ክልል ጉዳይ ብቻ ነው እንዴ? «አንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች» ስለኮኮቧ ጉዳይ አይመለከታቸውም እንዴ? «ለዚህ ጥያቄ ምላሽ እፈልጋለሁኝ፡፡» ስል የሰማ አንድ ወዳጄ «የአንዳንድ ህብረተሰብ ክፍሎች ብሔረሰብ ተወካይ በስራ ስለተጠመዱ ነው፡፡» ብሎኛል፡፡ ምላሹ አግቦ ይሁን አግባብ አለየም፡፡

ወዳጄ ይህንን ያህል ስለ ሰሞናችን ካወራን ይበቃናል፡፡ አሁን ከላይ በርዕሳችን ያነሳነውን ጉዳይ «እህ....» ተባብለን የምናወጋበት ቦታ ላይ ደርሰናል፡፡ እና እንቀጥል፡፡ «ቡሄን ለልማት እንዴት? እና ለምን?» (የዛ የትልቁን ጋዜጣ ርዕሰ አንቀፅ አስመሰልኩት አይደል?)

ባለፉት ዓመታት እንደ ፋሽን ተይዞ የነበረ ነገር ቢኖር «እንትን ለልማት!» የሚለው መፈክር ነበር፡፡ የዛኔ በርካታ ነገሮች ለልማት ይውሉ ዘንድ ተፎክሯል፡፡ (አንዳንዶች ተፎክሯል የሚለውን ተፎግሯል ብለው ሊያነቡ እንደሚችሉ የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ ይጠረጥራል፡፡ ጠርጥሮም ዝም አይልም «ተዉ እንዲህ ማለት አይገባም፡፡» ሲል ይመክራል፡፡) ታድያ ያኔ ሁሉም እንቅስቃሴዎች ለልማት ይዋሉ ተብሎ ሲፎገር (ይቅርታ ደረግልኝ ሲፎከር ማለቴ ነው) ቅድሚያውን ይዞ የነበረው «እድሮች ለልማት» የሚለው ነበር፡፡ ከዛ በኋላ ምን ያህል እድሮች ተሳክቶላቸው የልማት ተሳታፊ እንደሆኑ እርግጠኛ ባልሆንም እኛ ሰፈር ግን ዛሬም «የአቶ ጓንጉል እድርተኛ የሆናችሁ... ቀብሩም በስምንት ሰዓት ነው!» ከማለት የዘለለ ልማት ሲያለሙ አላየሁም፡፡ ቀስ በቀስ ከቀብር መልስ ወደልማት ሊመለሱ እንደሚችሉ ግን እምነቴ የፀና ነው፡፡

ለነገሩ እንደው በርዕሴ ቡሄ ለልማት ስል ትዝ ብሎኝ ስለ «እድር ለልማት» አወራሁኝ እንጂ በእድር ላይ የሚያጠነጥን ጨዋታ ይዤ አልመጣሁኝም፡፡ እልቅስ ቡሄን ለልማት ለምን አናውለውም የሚል ሃሳብ አለኝ፡፡ እስከዛሬ ቡሄ ጨፋሪዎች «የጋሽዬ ቤት ወርቅ ይፍሰስበት» በማለት መልካም ሲመኙ ኖረዋል፡፡ ጥሩ ነው መልካም ምኞት የሚበረታታ እንጂ ክፋት የለውም፡፡ ግን ግጥሙን ወደ ልማታዊ ግጥም ለመቀየር ያስችል ዘንድ ትንሽ ማሻሻያ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ወርቁ (በጋሽዬ ቤት ይፍሰስ የተባለውን ማለቴ ነው) ቫት የተከፈለበት መሆን እንዳለበትም አብሮ በማመልከት  ቡሄን ለልማት ማዋል

ይቻላል። ለዚህም ዝም ብሎ ወርቅ ይፍሰስበት ከማለት ይልቅ «እዛ ማዶ አንድ ቤት እዚህ ማዶ ሌላ ቤት የኔማ ጋሼ ይከፍላሉ ሻት!» የምትል ስንኝ ብንጨምርበት ቡሄውን ልማታዊ ቡሄ አደረግነው ማለት ነው። በተለይ ሰሞኑን ማንኛውም ግለሰብ የእጅ አሻራውን እንዲሰጥና ግብር ከፋይነቱን እንዲያረጋግጥ ከመኪና አሎ አሎ እስከ ቴሌቪዥን ማስታወቂያ እየተወተወተ ነው። ግና ቡሄን ለዚህ ቅስቀሳ ብናውለው የተሸለ ውጤት እንደሚኖረው አስባለሁኝ። «እዛ ማዶ አንድ ካራ እዚህ ማዶ አንድ ካራ የኔማ ጋሼ ሰጡ አሻራ» በማለት ቡሄን ከኪራይ ሰብሳቢነት ባህሪ ወደ ልማታዊ ባህሪ ልንቀይረው ይገባል። አባይን ለልማት መጠቀም ቢያቅተን እንዴት ቡሄን ለልማት መጠቀም ያቅተናል? የሚል አገራዊ ቁጭት ነው ለዚህ ሃሳብ ያነሳሳኝ። ከላይ እንደተገለፀው አንዳንድ ፅንፈኛ ቤተሰቦች ያሏቸው ልጆች መብራት ሃይል «ሃይል ቆጣቢ አምፖል» የማደል ስራ መስራቱን ሳያመሰግኑ እና «ሃይል ቆጣቢ አምፖል» በነፃ መታደሉን በማድነቅ ፈንታ ለልጆቻቸው «አረ በቃ በቃ መብራት በፈረቃ» የሚል ኪራይ ሰብሳቢ ግጥም አሰናድተው ሲያዘፍኑ ሰምቻለሁኝ። (እኒህ ፅንፈኞች ሃይል በሌለበት ሃገር ሃይል ቆጣቢ አምፖል ምን ያደርጋል? ሲሉም ይደመጣል።) ታድያ እኔም በበኩሌ «እዛ ማዶ አንድ አለም እዚህ ማዶ አንድ አለም የደቀንነው ሳፋ እኮ አይደለም» በሚል የሆያሆዬ ግጥም ልክ ልካቸውን ነግሬያቸዋለሁኝ።

እውነቱን ለመናገር ለሀገር አሳቢ ነን ካልን፣ የሀገሬ ጉዳይ ይመለከተኛል ካልን፣ በሃገሬ ልማት ላይ ተሳትፎ ማድረግ እሻለሁኝ ካልን ቡሄ ጥሩ አጋጣሚ ነው። ለምሳሌ ሙስናን ለመዋጋት ትረዳለች ብዬ ያሰብኳት ይቺን ግጥም ለሰፈሬ ልጆች አስጠንቻለሁኝ። «እዛ ማዶ አንድ ሳሙና እዚህ ማዶ አንድ ሳሙና የኔማ ጋሼ አይበሉም ሙስና» የምትል። በርግጥ በሙስና የሚጠረጠሩ ሰዎችን የመለየት ጥበብ ለልጆቹ ማስተማር ባለመቻሌ እንኳንስ ሙስና ቀርቶ ቁርስ ምሳ እራቱን በአግባቡ የማይበላ ምስኪን ደጃፍ ላይ ሁላ ግጥሙን ሊያወርዱት እነደሚችሉ ቢጠረጠርም አላፊ አግዳሚው ጆሮ መግባቱ በራሱ ቡሄን ለልማት እንደተጠቀምነው የሚያሳይ ነው።

ሌላው የዘንድሮን ቡሄን ልማታዊ ብቻ ሳይሆን ህጋዊ ማድረግም ይገባል ስል አስባለሁኝ ከዚህ በፊት በእንዝላልነት «እዛ ማዶ አንድ አንባሻ እዚህ ማዶ አንድ አንባሻ የኔማ ጋሼ ሻምበል ባሻ» ይባል ነበር። ሆኖም በተለይ በቅርቡ ከወጣው አዲሱ የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ አንፃር «ሻምበል ባሻ» ሲባል ምን አይነት ሻምበል ባሻ? ጥቅሙ የተነካ የደርግ ሻምበል ባሻ? ወይስ «ባለስልጣን ለመግደልና መንግስታዊ ተቋም ለማውደም ያሴረ ሻምበል ባሻ?» ይህንን ለመለየት ስለሚያስቸግር በደፈናው «እዛ ማዶ አንድ በራሪ እዚህ ማዶ አንድ በራሪ የኔማ ጋሼ ህግ አስከባሪ» በሚል ግልፅ ትርጉም ባለው እና ህጋዊ በሆነ ግጥም መተካት አለበት። ከዚህ ከህጋዊነት ጋር በተያያዘ ሌላም የማስበው ነገር አለ። የቡሄ ጨፋሪዎች ከሚያገኙት ገቢ ለመንግስት ግብር ይክፈሉ። ይቺ ናት ቡሄ ለልማት!!

**በመጨረሻም:-**

ሰሞኑ የተማሪዎች የምረቃ ወቅት ነው:: በመጀመሪያ ተመራቂዎችን እንኳን ለዚህ አበቃችሁ ማለት ተገቢ ነው:: ማሳሰቢያ:- ቀጥሎ የሚቀርበው ጨዋታ እናንተን አይመለከትም::

በአንዱ ከተማ ዩኒቨርስቲ ሲማር ቆይቶ ወደ ትውልድ ቀዬው የተመለሰ አንድ ወጣት ያጋጠመው ይህንን ይመስላል:: ይህ ወጣት በልጅነቱ በገጠር ትምህርት ቤት አልነበረምና ከተማ ውስጥ ትምህርት ሲያሳድድ ከርሞ ዩኒቨርስቲ ሲበጥስ ደግሞ የባሰ ሌላ ከተማ ቆይቶ ወደ ትውልድ መንደሩ ተመለሰ:: በዚህ ጊዜ አንድ አባት አህያቸውን እየነዱ በመንገድ ሲሄዱ አገኙትና «እባክህን አህያዬን አጫጭነኝ» አሉት ባለታሪካችን ከተማ ፊደል ሲለቅም የኖረ ነውና አልቻለበትም:: ባለ አህያው ተበሳጭተው «ዲግሪ ጫንክ ያሉኝ የእንቶኔ ልጅ አይደለህም እንዴ?» አሉት- ትኩር ብለው እያዩት:: «አዎ ነኝ» አላቸው:: ሰውየው በጣም ተበሳጭተው «ስንት አመት ሙሉ ከተማ ትምህርት ብለህ ከርመሃል:: ታድያ እንዴት አንድ አህያ መጫን ያቅትሃል?» ሲሉ ቢጠይቁት ወጣቱ ፈገግ ብሎ «አህያ መጫን እኮ አያስተምሩንም::» አላቸው:: ከቀናት በኋላ ከወዳጆቹ ጋር ባለ አህያው የሰነዘሩትን ወቀሳ ሲያወጋ አንድ ወዳጁ ይህንን ተናገረ:: «ሰውየው እውነት ብለዋል:: በዘንድሮ የትምህርት ፖሊሲ፤ ከዚህ በላይ ምንም ልንሰራ አንችልም::»

እኔ የምለው ይሄ የትምህርት ፖሊሲ ነገር እንደሚወራው ነው እንዴ!?

አሁን እንሰነባበት::አማን ያሰንብተን!

# የቴዲ አዲሱ የነፃነት ጉዞ

**በአቤል ዓለማየሁ**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሚትዎሮሎጂ ባልደረባዋ ፎርካስተር «ቤተልሄም አቢ» የቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) ከማረሚያ ቤት በሁለት ዓመት ገደብ በአመክሮ የመፈታት ዜናን ስትሰማ ደስታዋን መቆጣጠርና ማቆም አልቻለችም:: ቤቴልሔም ድምፃዊው ማረሚያ ድረስ ሄዳ ባትጠይቀውም፣ ከችሎት ታድማ የፍርድ ውሎውን ተከታትላ ባታውቅም መገናኛ ብዙኃንን በመጠቀም፣ ለጉዳዩ ቅርበት ሊኖራቸው ይችላሉ ብላ የምታስባቸውን ሰዎች በማሰስ የቴዲ ውሎና አክራሞት ምን እንደሚመስል ለማወቅ ትጥራለች::

«ሁሉም ዘፈኖቹ ትርጉም አላቸው:: «እንዴት አሰበው» ብለህ ትገረማለህ:: እስቲ ላምባዲናን ተመልከት» ስትል አብልጣ የምትወደውን የቴዲን ዜማ ጠቅሳ እይታው እንደሚያስገርማት ትናገራለች:: «በቃለ-ምልልስ ወቅት ሲጠየቅ የሚመልሳቸው መልስዎች ምን ያህል ምጡቅ እንደሆነ ያሳይሀል:: የሚጠቀምባቸው ቃላት መንፈሳዊና እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ ናቸው:: ይህን በሌላ በማን ድምፃዊ ላይ ትመለከታለህ?» ስትል ራሷን ጠይቃ መልሱን ሙሉ ሊያደርግላት ወደሚችለው «ቴዲ አፍሮ» በአይነ ህሊናዋ ታማትራለች::

## «አንድ ዓይነት ቴዲ»

ቴዲን ካወቀው 15 ዓመት ሞልቶታል፡፡ በ1988 «ይኼን ልጅ ሞክረው፣ ወደ ፊት ትልቅ ነገር ሊሰራ የሚችል ነው» ብላ አዳነች ወ/ገብርኤል (አርቲስት) ወደ እርሱ ስትልከው አምኖ አብሮት እንዲሰራ ለመፍቀድ ብዙ አላመነታም፡፡ «ገና እንዲሞክር ማይክ ስንሰጠው ድምፁ ተመቸኝ፡፡ አብሮን መስራት እንደሚችልም ነገርኩት» ይላል ድምፃዊና ጊታሪስት ዳዊት ጽጌ በቴዲ ብቃት እምነት ለማሳደር ተደጋጋሚ ሙከራዎች እንዳላስፈለጉት ሲገልጽ፡፡

ቴዲ አፍሮ የመጀመሪያ አልበሙን (አቦጊዳን) ለህዝብ ሲለቅ ለማስታወቂያ የሚውል ምስክርነት እንዲሰጥ ዳዊትን ሲጋብዘው «እሺ» ብሎ በመቀበል «ቴዲን ካደነቅኩት ቆይቻለሁ» ሲል መጀመሪያ ወዳገኘበት ቀን እየተመለከተ ምስክርነቱን ሰጠ፡፡ «ትላንት የማወቀው ቴዲ ከመታወቁና ከመግነኑ በስተቀር አንድ አይነት ቴዲ ነው፡፡ አልተለወጠም፡፡» ይላል  አቀንቃኙ ዝና እንደማይለውጠው ሲናገር፡፡

ዳዊት ጽጌ «በጣም ነው እምወድሽ» የተሰኘ ሁለተኛ አልበሙን በትላንትናው እለት መለቀቅን ግጥምጥሞሹን በሙያው እንዲዳብር ካደረገው የሙያ ጓደኛው ቴዲ አፍሮ መፈታት ጋር አያይዞት እንደሆነ ይጠይቁታል፡፡ «ብዙ ሰው እንደዚህ ብሎ ጠይቆኛል፡፡ ሁኔታው ሆን ተብሎ የተደረገ ይመስላል፡፡ ግን አጋጣሚ ነው፡፡ አሜሪካ የተለቀቀው ረቡዕ (ከቴዲ መፈታት 1 ቀን አስቀድሞ) ነው፡፡ እዚህ የነበሩትን የማስታወቂያ ስራዎች ስላላጠናቀኩኝ የለቀቅኩት ዘግይቼ ነው፡፡»

የሚወጡ አዳዲስ ስራዎች በአድማጩ ተቀባይነት አለማግኘትም ሆነ ፍራቻ ውጦት የቀዘቀዘቀው የሙዚቃ ኢንዱስትሪን ከኢኮኖሚ ጋር የሚያያይዘው ዳዊት በኑሮ ወድነት የተነሳ ሰው ሙዚቃን የሚያስቀድመው አንደኛ እና ሁለተኛ ነገር አለመሆኑን ይስማማበታል፡፡ «ከጋሽ ጥላሁንና ማይክል ጃክሰን ሞት በኋላ የድምፃዊያኑ ስራዎች በብዛት ተሰምተዋል፡፡ ቴዲ ሲፈታ ዘፈኖቹ በተለያየ ቦታና ሙዚቃ ቤት ይሰማሉ፡ ቴዲ ነገ ስራውን ቢለቅ መስማቱን ለአፍታ ባልጠራጠርም ገበያው ላይ የሚያመጣውን ተጽኖ ግን እርግጠኛ ሆኜ መናገር አልችልም፡፡» ሲል ከ5 ዓመት በላይ የቆየበትንና የኮፒ ራይት ህግ አለመከበር ጥላ ያጠላበትን የሙዚቃ ቤት ስራ ዋቢ አድርጐ ጠቅሷል፡፡ ዳዊት የቴዲ መፈታት ለድምፃዊውና ለቤተሰቡ ብቻ ሳይሆን ለሙዚቃም «የምስራች» መሆኑን ለአውራምባ ታይምስ ገልጿል፡፡

## መስተንግዶ አዋቂ

ሐሙስ ማምሻውን የቴዲን መፈታት የሰሙ የልብ አድናቂዎች ቴዲ ከሚገኝበት የእናቱ ቤት ሲደርሱ በር ላይ የነበረው ትርምስና ዘልቆ መግባት መገደቡ አሳዝኗቸው የተመለሱ ብዙዎች ናቸው፡፡ ቴዲን አስመልክታ በተለያዩ የህትመት ውጤቶች ላይ ግጥሞች የምትጽፈው ህይወት ታከለም ከበር ማለፍ ካልቻሉታና ካዘኑት ውስጥ አንዷ ናት፡፡ «ዋናው ነገር ቴዲን የማየትና ያለ ማየት አይደለም፡፡ ባለንበት ስራዎቹን ማጣጣም እንችላለን፡፡ ከተለያየ ቦታ ያመጣን ፍቅር መሆኑን የበር ላይ ጠባቂዎቹ ሊረዱት ይገባ ነበር፡፡» ትላለች፡፡ ህይወት በሁኔታው ብታዝንም በቴዲ ላይ ግን ቂም አልያዘችም «ሰዎች ባጠፉት እሱ ተጠያቂ የሚሆንበት ምክንያት የለም፡፡»

ሐመስ በሩን አልፋ መግባት ያልቻለችው ህይወት ብቻ አይደለችም፡፡ የቴዲን የፍርድ ውሎ ያለመታከት ሲዘግቡ የነበሩ የህትመት ሚዲያው ባልደረቦችም ጭምር እንጂ፡፡ ይህ ሁኔታን ቴዲ የሰማና የተረዳ ይመስላል፡፡ ቅር ተሰኝተው የተመለሱ ጋዜጠኞችንና አድናቂዎቹን ከበር በአግባቡ እየተቀበለ አስተናግዶ ስቆ ይሸኛል፡፡ «ለስላሳ አምጡለት... ጾም ቢሆንም ጥሩ ሽሮ አለ፡፡» በማለት ከወዲያ ወዲህ እየተንጐራደደ እንግዶቹን ያስተናግዳል፡፡

## እውቅናን ማባረር

የድምፃዊው ሁለት ጠበቆች ሚሊዩን አሰፋና አምኃ በልጉ የሚቆሙባቸውን የወንጀል ችሎቶች ላይ በአጋጣሚ ከታደመ አሊያም የስራ ግንኙነት ካለው ሰው በስተቀር የሚታወቁና «Public Figure» የሚባሉ ግለሰቦች አልነበሩም፡፡ (በእርግጥ ጠበቃ ሚሊዮን በምርጫ 97 በቴሌቭዥን መሰኮት ቀርበው ተቃዋሚዎችን ሲያንቋሽሹ እንደነበርና አዲሱን የፕሬስ ህግም ከአቶ ሽመልስ ከማል ጋር ሆነው ያረቀቁ እንደመሆናቸው ብዙ ጊዜ በቴሌቭዥን የመቅረብ እድል አላቸው፡፡)

ጠበቆቹ ጥብቅና የቆሙለት ሰው በኢትዮጵያ ሙዚቃ ውስጥ አብዮት ያስነሳ የዝናው መጠን ከጫፍ የደረሰ ድምፃዊ እንደመሆኑ ትኩረትና የሚዲያ ሽፋን አግኝተዋል፡፡ በተለይ ከመጀመሪያው የችሎት ውሎው አንስቶ ጉዳዩን ከያዙት የድምፃዊው የህግ አማካሪ ጠበቃ ሚሊዮን አሰፋ በበለጠ (እጅግ በጣም በበለጠ) ጉዳዩ ህዝብ የሚከታተለውና ሊያውቀው የሚገባ መሆኑን በመገንዘብ ለመገናኛ ብዙኃን ተገቢውን መረጃ በማቀበል ጠበቃ አምኃ የተሻሉ ነበሩ፡፡ መገናኛ ብዙኃንን በአግባቡ መጠቀምና ድምፃዊውን የተመለከቱ የህግ ጉዳዮች ላይ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ለማስረዳት ደከመኝ ማለት፣ ቁጣና ንጭንጭ አያውቁም፡፡ በአንጻሩ ግን ጠበቃ ሚሊዮን (ለኢትዮቻናልና ሪፖርተር ካልሆነ) እንደ አውራምባ ታይምስ ላሉ ጋዜጦች አንዳች መረጃ አይሰጡም ጥያቄ ሲቀርብላቸውም መረጃ ከመስጠት ይልቅ ቁጣና ዘለፋ ይቀናቸዋል፡፡

የቴዲ እናት ወ/ሮ ጥላዬ አራጌ፣ ድምፃዊውን በቅርብ የሚያውቁት ወዳጆቹ ከነበራቸውና ካላቸው ሙያ በበለጠ ቴዲን ማእከል አድርገው በሚወጡ ዘገባዎች የበለጠ እውቅናን አግኝተዋል፡፡

ጥቂቶች ደግሞ አሳደው ያገኙትን «እውቂያ» በመጠቀም «ዋጋ» የማታወጣ ኩራት ቢጤ ደርበዋል፡፡ ሌሎች ደግሞ ዋሾ ሆነው «ለምን ይዋሻል?» ሲሉ የእሱ ዘፈኖች ላይ ብቻ ለመዝመት የቆረጡ መስለው ያባረሩትን እውቅና ሳይሆን ጥላቻን ሰፍረዋል፡፡

## ሙዚቃ ነቃ

የኮፒ ራይት መብት በአግባቡ አለመከበርን ፈርተው «ማስተር» ሸጠው ና ገዝተው የተቀመጡ ድምፃዊያኑንና ባለ ሙዚቃ ቤቶች ተበራክተዋል፡፡ «ይሁን» ብለው ደፍረው የሚወጡ የሙዚቃ አልበሞችም የአድማጩን ትኩረት መሳብ አልቻሉም፡፡ በረዷማውን የሙዚቃ ገበያ እንዲነቃ ብዙዎች የቴዲ አፍሮን የሙዚቃ ስራ (አልበም) ይጠብቃሉ፡፡ «ቴዲ አሁን ሁለት ፈተና አለበት፡፡ የቀዘቀዘውን ኢንዱስትሪ ያሞቃል ብለው ለሚጠብቁት አድማጮች ስራ ሠርቶ ማቅረብና «ከውጪ ዜማዎች ላይ ወስዶ

ይሰራል» ለሚሉት ምላሽ ለመስጠት የራሱ የሆኑ ወጥ ስራዎች መስራት ናቸው:: ይህንን ለማድረግ በነበረበት ቦታ አንፃር በቂ ጊዜ ሊወስድ ይገባዋል» ይላሉ:: አንድ የሙዚቃ ባለሙያ::

**«ቶሎ በል»**

አድናቂዎቹ «ቴዲ ከመታሰሩ በፊት ስራዎችን አጠናቋል» የሚል ወሬ ስለሰሙ የቴዲን ቀጣይ አልበም ለመስማት ቢቸኩሉም እሱ ግን አልበሙ ለህዝብ የሚያደርስበትን ጊዜ አያውቀውም:: በግምት ቀኑን መናገርም አልፈለገም:: በቴዲ ስራዎች ፍቅር ያበዱት ፎርካስተሯ ቤተልሄም፣ ግጥም ፀሐፊዋ ህይወት እና መላው አድናቂዎቹ ቴዲ አሁን ነፃ ነውና በነጠላ ዜማ ወይም በአልበም ስራው እየጠበቁት ነው:: «ምን አዲስ ነገር ይፈጥር ይሆን?» እያሉ::

# እስኪ እንደገበያው መርህ እንኑር

**በእሴኒ ዘውዴ ገብረመድህ *(ዶ/ር)***

የኢትዮጵያን ምርት ገበያ (Ethiopia Commodity Exchange) አስመልክቶ አመክንዮዓዊነት ከተላበሰ ውይይት ጋር አንዳች ተያያዥነት ባይኖረውም፣ በቅርብ ስለእኔ የብሔር ማንነት ብዙ ተብሏል:: ነገር ግን፣ ዝባዝንኬ አስፈላጊውን ሊያጠለሽ ጥልቅ ሲል፣ ምላሽ መስጠት ግድ ይላል - ምንም እንኳን ምላሹ የፈለገ ሳቢ ላይሆን ቢችልም::

ኢትዮጵያዊ ነኝ፣ ያ በራሱ እውነተኛና እጅግ አስደሳች እንደመሆኑ መጠን ማንም ማንነትቴን ሊገልጽ፣ ሊያቀል ወይም በተቃራኒው ለመግፈፍ መብት የለውም:: ማናችንም ብንሆን፣ እያንዳንዳችን፣ በእግዚአብሔር የተሰጡ በተለየ የሚገልፁን በርካታ ክስተቶች አሉን፤ ስለዚህም፣ ስለማንነቴ አልፀፀትም ወይም አልሟገትም::

ተጨባጩ እውነታ ምንድነው፣ ውልደቴ አዲስ አበባ ውስጥ ነው፤ ከኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣሁትም በአራት ዓመቴ ሲሆን አካሄዴም ለንጉሳዊው መንግስት ግልጋሎት የሰጠውንና በወቅቱ የተ.መ.ድ ከፍተኛ ባለስልጣን የነበረውን አባቴን ዘውዴ ገብረመድህንን በማጀብ ነበር:: በአሜሪካ ከጥቂት ዓመታት ቆይታ በኻላ ጉዞ ወደ አገር ቤት ሆነ፤ ከዚያም የአዲሱን የደርግ ሥርዓት ውጥንቅጥ ሽሽት ቤተሰቤ ዳግም ኢትዮጵያን ነቅሎ ወጣ፤ በዚህ ጊዜ የተጓዝነው ወደአሜሪካ ሳይሆን ወደ ሩዋንዳና በኋላም ወደ ቶጎ፣ ማላዊና ኬንያ ነበር:: በመሆኑም፣ እድገቴ በስድስት የተለያዩ አገሮች ውስጥ ነበር - ፈረንሳይኛንና እንግሊዝኛን እየለዋወጥኩ እየተማርኩና እግረመንገዴንም ስዋህሊ ቋንቋን አጠናሁ::

በእነዚህ ዓመታት፣ ለጠቅላላ ስኬቶቼ ውለታ የዋሉልኝ ወላጆቼ፣ እኔና እህቶቼ ለአገራችን ኢትዮጵያ ጥልቅ ፍቅርና ኩራት እንዲያድርብን አድርገው አሳድገውናል:: በተለያዩ አገራት፣ የወጣትነት ማንነቴን ለመረዳት እየታገልኩ በቆየሁባቸው ዓመታት፣ ወላጆቼ ስለቅርሴና ስለአያቶቼ የነገሩኝን ታሪኮች አጣጥማቸው ነበር:: ስለምትወዳት ሀረር ኩራቷን ለመግለጽ ዕድል ያገኘች እንደሆነ ያ ዕድል ጭራሽ አምልጧት የማያውቀው እናቴ ብዙወርቅ በቀለ፣ ውልደታቸው መንዝና ጎንደር ስለሆኑት፣ ከጣሊያን ወረራ በኋላ በገጠራማ ሀረርጌ ስለኖሩት፣ የአገራቸውን መሬትና ስድስት ልጆቿን ለመታደግ በወራሪው ጣሊያን ላይ ከተነሱት ጥቂት ሴት አርበኞች መካከል አንዷ ስለነበሩት አስደማሚዋ አያቴ እማሆይ ሳባ ይፋት ታሪኮች ታወጋኝ ነበር፤ እንዲሁም፣ በሀረርጌ ከተማ የተከበሩ ዳኛ ስለነበሩትና ውልደታቸው ከጉራጌና ከአማራ ቤተሰብ ስለነበሩት አያቴ አቶ በቀለ ኃይሌም:: ልጅ ሳለሁ፣ በሳል ተናጋሪ፣ አዋቂና ቆራጥ ከነበሩት ሴት አያቴ እማሆይ በለጥሻቸው ኃ/ጊዮርጊስ ጋር ለሰዓታት ተቀምጦ ማውጋት አይሰለቸኝም ነበር:: እናቴን ጨምሮ እማሆይ በለጥሻቸውና የተቀሩት ልጆቿ አቀላጥፈው በሚናገሩት ኦሮምኛ በጂጂጋ፣ ፌዲስና ደደር አካባቢዎች - አሁን ድረስ ዘመዶቼ የሚገኙበት - ስለነበሯቸው የቡና ማሳሳዎች በፈገግታ ታጅበው ያጫውቱኝ ነበር::

አባቴ በበኩሉ፣ በአብዛኛው የሴት ልጆቹን ቀልብ ለመቆንጠጥ፣ ሩዋንዳ ኪጋሊ በተ.መ.ድ በተሰጠን መኖሪያ ቤት የነበረውን የውኃ ማጠራቀሚያ ጋን፣ «ቡልጋ ምንጭ» በማለት ሰይሞት ነበር - አባቱ የተወለደበትን ሰሜን ሸዋ ለመዘከር:: በንጉስ ምንሊክ ዘመን የተከበሩና ከፍተኛ ሥነ-ምግባር ስለነበራቸው አያቴ ፊት-አውራሪ ገብረመድህን በኩራት ያወራላቸው ነበር:: ፊት-አውራረ ገ/መድህን፣ በ19ኛው መቶ ክ/ዘ መጨረሻ አካባቢ፣ የታላቁ የወላይታ ንጉስ ንጉስ ጦና ወንድም ልጅ የነበሩትን (አያቴን) ወ/ሮ አየለች አላያን አግብተው ኑሯቸውን እዛው እንደመሰረቱ ታሪካቸውን አጫውቶኛል:: በ7 ዓመቴ፣ የአባቴን የትውልድ ስፍራና አሁን ድረስ አብዛኞቹ ዘመዶቼ የሚኖሩበትን ሶዶ መጎብኘቴ ይታወሰኛል - በወቅቱ 100 ዓመት ከሚሞላቸው አያቴ ጋር የቀሩትን የመጨረሻቹን ዓመታት አብረን ለማሳለፍ ነበር ወደ ሶዶ ያቀናነው:: ለግላጋ፣ ኩሩ፣ ወንዳወንድና ጥልቅ ሃይማኖተኛ የነበሩት አያቴ፣ ለእኔና ለእህቴ የቡና ማሳቸውን እያሳዩን በጣም ተወዳጅ ስለነበሩት ሴት አያቴና ስለልጆቿ እና አሁን ድረስ ቡልጋ ስለሚገኙት ዘመዶቼ ሲያወጉን አስታውሳለሁ:: ኒውዮርክ ሳለሁ ያወኳቸውን የሕፃናት ቀልዶች በእንግሊዘኛ ሳወጋ - ቋንቋውን ባለማወቅ - ደስበሚል ፈገግታ ይሰሙኝ እደነበር እንዲሁ የማስታውሰው ነው::

እንግዲህ ይህ ነው የእኔ ኢትዮጵያዊነት ታሪክ - እያንዳንዳችን ኢትዮጵያውያን ሊኖረን እንደሚችለው ልዩ የሆነ ታሪኬ:: ያ ነው የእኔ ኢትዮጵያ ታሪክ - ፍቅሬ የጸናላትና በተቻለኝ መንገድ ላገለግላት፣ የወጣትነት ዕድሜዬን ማሊ፣ ስዊዘርላንድና አሜሪካ በመኖሬና አሉ በተባሉ ጥቂት ምርጥ ተቋማት በመሰልጠኔና በመስራቴ፣ እንዲሁም በመላ ዓለም ወደ በርካታ አገሮች በመጓዜና በማሰሴ ያካበትኳቸውን፣

የቀረፁኝን ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች በጠቅላላ ሳፈስላት ከ30 ዓመታት በኋላ የተመለስኩላት የኢትዮጵያ ታሪኬ:: ይህች ናት የእኔ ኢትዮጵያ - ከዘመን ዘመን ደማቸው በውስጤ የሚኖር ጀግናና ፈርጣማ ወንዶችና ሴቶችን፣ መላ ቅርሴንና ቤተሰቤን የምትወክልልኝ:: ይህቺ ናት ኢትዮጵያዬ - ልሰራላትና ልዋደቅለት ፈቃደኛ የሆንኩላት እና ሁሉም ነገሮች የሚቻሉ መሆናቸውን የማምንባት:: ይህቺ ነች የእኔ ኢትዮጵያ - ሁላችንም እንደኢትዮጵያዊነታችን ያለንን ፍቅርና ኩራት ለማስረፅና የሰው ልጆች ትስስሮሽች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከሩ በሄዱባት ዓለማችን ኢትዮጵያውያን መሆናቸውንና እንዲሁም ዓለም አቀፍ ዜጎች እንደሆኑ ላስተምራቸው ያቀድኩላቸው አሜሪካ የተወለዱ ልጆቼን ያመጣሁባት::

ኢትዮጵያ የእኛው ነች - የእኛው ነሽ የምንላት፣ የምንገነባትና የቀድሞ ስፍራዋ የምንመልሳት:: ለልጆቻችን የተሻለ የወደፊት እድል በሕብረት ለመገንባት በአጥፊ የብሄር ጥላቻ ከመጠመድ ይልቅ ጠቅላላ ማንነታችንን ማዕከል ብናደርግ በእጅጉ የተሻለ ነው:: የእኔ ማንነት፣ ለጠቅላላ ኢትዮጵያውያን (የብሔራቸው ወይም ይገባኛል የሚሉት የአገሪቱ ጥግ ከግምት ሳይገባ) የተሻለ የገበያ ሥርዓት ለማምጣት ተነሳሽነቱን ለመምራት ለወሰድኩት ምርጫና ላለኝ ብቃት አንዳች የሚፈይደው የለም:: ከሁሉም በላይ ገበያ የሰዎች ቁርኝት ማለት ነው - ሁለት ወገኖችን የሚያገናኝ የምርቶችና የገንዘብ ልውውጥ የሚስተናገድበት:: ገበያ ገለልተኛ ነው - በሁለቱ ወገኖች በኩል ማን ነው ያለው የሚለው የማይመለከተው:: ወሳኙ ቁርኝቱ ነው:: በዓለም ሁሌም በጣም ፕራግማቲክ ሆነው የማገኛቸው ነጋዴዎች ናቸው:: እኛም በዚህ የገበያ መርህ እንኑር:- ትርጉም በሚያመጡ መንገዶች እርስ በእርሳችን ያለንን ቁርኝቶች ከገነባን፣ የበለጠ ሀብታሞችና የበለጠ ፈርጣሞች እንሆናለን:: እንደገበያ እንሁን:: ብቸኛው ተስፋችንም ነው የሚል እምነት አለኝ::

***/ዶ/ር እሌኒ ገብረመድህን የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ ናቸው/***

# ሁለቱ የጠ/ሚኒስትር መለስ ገጽታዎች

ኢትዮጵያን በጠቅላይ ሚኒስትርነት ከ1991 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ መርተዋል፣ ሆኖም ገና በ54ኛ እድሜያቸው ላይ የሚገኙት አቶ መለስ ዜናዊ ፣ ሁለት ገጽታዎች አሏቸው:: አንድኛው ድህነትን ከሚታገል መሪ ጋር ይመደባል:: በዚህ ገጽታቸው፣ 80 ሚሊዮን በላይ ከሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ 85 በመቶው በሚኖርበት ገጠራማው ክፍል አሳዛኝ ሁኔታዎችን በማሻሻል፣ በእንግሊዝ ቀዳሚነት፣ በምዕራብያውያንን መንግስታት ተሞግሰዋል:: አዳዲስ መንገዶችን፣ ክሊኒኮችንና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በመገንባት፣ እንዲሁም በበርካታ የግብርና ፕሮጀክቶቻቸው ይወደሳሉ:: በአገሪቱ የወንጀል መስፋፋትን በመቀነስና በተለይ በኃብት በኩል የፓርላማ አባላት ያኖራቸዋል በሚያስብል መልኩ በቂ ክፍያ እንዲከፋላቸው በማስደረጋቸውም አድናቆት ይቸራቸዋል:: በዓመት ደለብ ያለ ክፍያ - 120 ሺህ ዶላር - ከሚያገኙት የኬኒያ የፓርላማ አባላት ጋር ሲነፃፀር የኢትዮጵያ የፓርላማ አባላት የሚያገኙት ዓመታዊ ደሞዝ 3,240 የአሜሪካ ዶላር ብቻ ነው:: በተጨማሪ፣ ባለፉት ጥቂት ዓመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በፍጥነት አድጓል:: በዚህ ዓመት ኢኮኖሚው በ10 በመቶ እንደሚያድግ አቶ መለስ ተናግረዋል፣ ምንም እንኳን አይ.ኤም.ኤፍ. የዚህን ግማሽ ቢያስቀምጥም::

አእምሮአቸው ብሩህ ነው፤ የማስታወስ ችሎታቸው የትየለሌ ነው፤ እንዲሁም፣ በኃይልና በቁርጠኝነት የተሞሉ ናቸው:: ከስንት አንዴ በሚሰጡት ቃለ-ምልልስ፣ ካለአንዳች ማስታወሻ ሳያቋርጡ ለሁለት ሰዓታት ይናገራሉ:: በጠራ እንግሊዘኛ በሚናገሯቸው ጥልቅ ገለፃዎች የውጭ ለጋሾችን በእጃቸው ያስገባሉ:: ምናልባት፣ ርሀብ ወደፊት ሊከሰት ይችላል በሚል ፍርሀት ሊሆን በሚችል ምክንያት ስለርሀብ ባያወሱም፣ የምዕራባያውያኑን ህሊና ለመንካት ያለፉ አሳዛኝ ትውስታዎችን ይጠቀማሉ:: እርዳታ ለኢትዮጵያ ማቅረብን ግድ ያስባለው የ1984 ርሀብ በአውሮፓ መበከል ሳቢያ ምናልባት የተባባሰ ሊሆን እንደሚችል ባለፈው ወር ጠቁመው ነበር:: በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ካሳ ምዕራቡ ዓለም በዓመት 40 ቢሊዮን ዶላር ለአፍሪካ ሙሉ በሙሉ ይከፍላል ብለው እንደሚጠብቁ አቶ መለስ ይናገራሉ::

ይሁንና፣ ከማርክሲስት ተፋላሚነታቸውና ካላቸው የሰብዓዊ መብቶች አጠባበቅ ሪከርድ ጋር ጠንካራ የፖለቲካ ሰው የሆኑት አቶ መለስ፣ የልዩነት ሀሳቦችን ለማስተናገድ የማይፈቅድ ሌላ ገጽታም አላቸው:: በ1997 ከተካሄደው አወዛጋቢ አጠቃላይ ምርጫ ማግስት በተከሰተ አለመረጋጋት የጸጥታ ኃይሎቻቸው 200 የሚደርሱ ሲቪሎችን ሕይወት አጥፍተዋል:: ቀውሱን አስመልክቶ በተቋቋመው ገለልተኛ አጣሪ አካል የሰሩ አያሌ ዳኞቹ አገር ለቀው ለመሰደድ በቅተዋል:: በሆነ ወቅት የተማሪዎች ንቅናቄ አስተባባሪ የነበሩት አቶ መለስ፣ ተማሪዎችን ለመቆጣጠርና ፍርሀት ለመዝራት በየዩንቨርሲቲዎች ሰላዮችን ይበትናሉ፣ ገለልተኛ ጋዜጣዎችን ይዘጋሉ፣ እንዲሁም የሚያስጨንቋቸውን ስቪክ ማህበራት በማገድ በእርዳታ ፕሮጀክቶች ውስጥ ጣልቃ ይገባሉ:: ባለፈው ወር ሶማሌዎች በሚኖሩበት የአገሪቱ ክፍል 40 አካባቢ የሚሆኑትን ከእንቅስቃሴያቸው አግደዋቸዋል::

ከ97 ምርጫ በኋላ አያሌ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ አመራሮች በአገር ክህደት ክሶች ወህኒ ቤት ወርደው ነበር፤ ከዓመትና ከዚያም በላይ የእስር ቆይታ በኋላ ተለቀቁ:: አሁንም ግን ዳግም የታሰሩ አሉ:: በቅርቡ የጸደቀ አዲሱ ሁሉን-ያዥ ሕግ፣ ሽብርተኝነትን በማበረታታት በሚል ክስ ሰላማዊ ተቃዋሚዎችን ተጠያቂ ሊያደርግ የሚችል ነው::

ኢኮኖሚው፣ አቶ መለስ እንደጠቀሙት ያን ያህል ተስፋ ሰጭ አይደለም:: ኢትዮጵያ ለጥቂት ጊዜ የሚበቃት የውጭ ምንዛሪ ይኖራት ይሆናል:: በንግዱ ዘርፍም አገሪቱ በጣም ኋላ ቀር ሆና ቀርታለች:: በአፍሪካ፣ ኢትዮጵያውያን በተንቀሳቃሽ ስልክ ባለቤትነት በዝቅተኛ ደረጃ ከሚጠሩት መካከል ይመደባሉ:: የባንክ አሰራር አልዘመነም:: አሁን ድረስ፣ የእርሻው ዘርፍ፣ ከእጅ ወደ አፍ ከመሆን አልዘለለም::

እናም፣ ዳግም የርሀብ ጉዳይ አሳሳቢ ሆኗል:: ሆኖም አቶ መለስ፣ ዓይኖቻቸውን ጠበብ በማድረግ በጎርናና ድምጽ፣ «ያ ውሸት ነው፤ ፍፁም ውሸት::» ነው ይላሉ:: ሕዝቡን ለመመገብ በመንግስት መጋዘኖች ውስጥ ከበቂ በላይ ምግብ መኖሩንም ተናግረዋል:: ነገር ግን፣ መጠባበቂያ የእህል ክምችቱ ለሕዝቡ እንዲከፋፈል ቀድሞውኑ ተወስኖ እንደነበር ሌሎች ይናገራሉ:: የተ.መ.ድ.ና የውጭ በጐ አድራጐት ድርጅቶች በሕዳር፣ በትግራይ ከፍተኛ ርሀብ ይከሰታል ብለው እየተነበዩ ነው:: ከአገር ውስጥ ተጨማሪ አቅርቦት ሊገኝ ካልተቻለ ቢያንስ ስድስት ሚሊዩን ሕዝብ የምግብ እርዳታ ሊያስፈልገው ይችል ይሆናል::

አብዛኛዎቹ የአቶ መለስ ሹመኞች፣ ለትችቶች ትዕግስት የሌላቸውና የጨነቃቸው ይመስላሉ:: ከጦር ሰራዊቱ ውስጥ ቅሬታ ከሚያሰሙትም ሆነ ከኢትዮጵያ ባለብዙ ቀለም ሕዝቦች መካከል ቅያሜ ከተሰማቸው የብሔር ቡድኖች የሚነሱ የአገራቸውን ስጋቶች አጋንኖ ለማቅረብ ጠ/ሚኒስትሩ ፈጣን ናቸው:: በዚህ ዓመት መጀመሪያ ኦነግ በግንባታ ላይ በነበረ ግድብ ላይ ጥቃት ማድረሱ በመንግስት ቴሌቭዥን ከተለፀ በኋላ ከቡድኑ ጋር በተያያዘ ሰዎች ለእስር ተዳርገዋል:: በተጨማሪ፣ በምስራቅ የአገሪቱ ክፍል የነዳጅ አሳሽ የውጭ ዜጐችንና የኢትዮጵያ ዜጎችን ሕይወት ያጠፋው ከኢትዮጵያ መገንጠልን ከሚያራምደው ኦብነግ ዘንድ ስጋቶች እንዳሉ የኢትዮጵያ መንግስት በተከታታይ መግለጫዎችን አውጥቷል::

አቶ መለስ፣ በአጠቃላይ ክልሉ ባሉት ክስተቶች ምክንያታዊ በሆነ መልኩ ተጨንቀዋል:: ኢትዮጵያ፣ የእናታቸው የትውልድ ስፍራ ከሆነችው ኤርትራ ጋር ያላት ግንኙነት መልካም እንዳልሆነ ቀጥሏል:: ኢትዮጵያን ለመጉዳት ያነጣጠሩ ጂሀዲስቶችን ስለመደገፏ [ኤርትራን] ይወነጅላሉ:: በተጨማሪም፣ ኦሮሞ አማፂዎችንና የኦጋዴንን ከኢትዮጵያ መገንጠልን የሚያቀነቅኑ ተገንጣዮች በመደገፏ አቶ መለስ ኤርትራን ይወነጅሏታል:: «የኤርትራ መንግስት ኢትዮጵያን ለማወክ ቆርጦ የተነሳ ነው፣» ይላሉ አቶ መለስ:: «ከነማን ጋር እንደሚዋዋል አይጨንቀውም::» ይሉታል የኤርትራን መንግስት::

እንዲሁም፣ በቀጠለው የሶማሊያ ቀውስ መረበሻቸው አልቀረም:: በ2006 (እ.ኤአ.) መጨረሻ፣ በኢትዮጵያ ላይ ጂሀድ አውጀው የነበሩ ኢስላሚስቶችን ለማስወገድ በአሜሪካ አይዞህ ባይነት ጦራቸውን ወደ ሶማሊያ አዝምተው ነበር:: ሰላም ማስፈን አልቻሉም በዚህ ዓመት መጀመሪያ አካባቢም ጦራቸውን ከሶማሊያ አስወጥተዋል:: ይሁንና፣ አቶ መለስ ሊያስወግዷቸው የፈለጓቸውን አል-ቃዒዳ መሰል ቡድኖችን በማሰማራት ጂሀዲስቶቹ ዳግም ቀድሞ የለቀቋቸውን መሬቶች እየተቆጣጠሩ ይገኛሉ::

ስለዚህም፣ ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ አቶ መለስ ተወጥረዋል:: አጠቃላይ ምርጫ በቀጣዩ ዓመት ይካሄዳል:: ከዚህ ቀደም ከቀጣዩ ምርጫ በኋላ ሥልጣን እንደሚለቁ ፍንጭ ሰጥተው ነበር:: ሆኖም በቅርቡ፣ እንዲህ ያሉ አስተያየቶች «አሰልቺ» እንደሆኑ አድርገው መግለፃቸው እርግጠኛነታቸው ሚዛን ያልደፋ አስመስሎታል:: አንዳንዶች የጠቅላይ ሚኒስትርነት ቦታውን ሊለቁ እንደሚችሉ፣ ነገር ግን ገዢውን የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲ ግንባር መምራታቸውን እንደሚቀጥሉ ይናገራሉ:: በየትኛውም መልኩ ይሁን ሙከራ ሊያደርጉ መቻላቸው ያመዝናል - በቀነሰ የልዩነት ሀሳብ::

# የኦርዌልያን ዴሞክራሲ

## «ሁሉም እንስሳት እኩል ናቸው፤ ነገር ግን አንዳንድ እንሰሳት ከሌሎቹ የበለጠ እኩል ናቸው::»

**በአየነው ኃይለሥላሴ**

በአንድ ወቅት የኢትዮጵያ ጠንካራ የነበረ ተቃዋሚ ፓርቲ አባላት በድጋሚ እርስ-በርሳቸው ተናንቀዋል፤ እናም አሁን ግን ለማመካኘት ጣታቸውን የሚቀስሩበት ተወቃሽ የላቸውም:: ግጭታቸውን አልፈው በአንድነት አንደሚቀጥሉ፣ ወይም ወደ ሁለት ፓርቲዎች እንደሚከፈሉ፣ አልያም ሁሉንም ነገር ትተውና ልዩነታቸውን ተቀብለው እንደሚቀጥሉ ገና ወደፊት የሚታይ ነው::

ሀገሪቱ ተግባራዊ አስተዋጽኦው (ከወራት በኋላ እንጂ) አሁን ሊታወቅ በማይችል አሳዛኝ የኢኮኖሚ ሁኔታ ውስጥ ትገኛለች:: በአሁኑ ሰዓት ሀገሪቱ በጥልቅ ችግር ውስጥ አትገኝም ለማለት አይደለም:: በዚህ ወቅት ያለውን የኢኮኖሚ ችግር የትኛውም ያህል የዴሞክራሲ መጠን በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሊፈታው አይችልም:: ነገር ግን በረዥም ጊዜስ? ጠንካራ ተቃዋሚ አለመኖሩ 80 ሚሊዮን ገደማ ወይም ቢያንስ 80 ሚሊዮን ህዝብ ላለባት ሀገር ለመጪው ጊዜ ጭንቅ የለም (the-devil-may-care ) አመለካከቶች እና ፖሊሲዎች ማረጋገጫ የሚሰጥ ይሆን?

ድንጋጌዎችን እና ፖሊሲዎችን ማን እንደሚያወጣ፣ በየትኛው መንገድ እንደምንሄድ ማን እንደሚወስን፣ እንደ ዜጐች እና እንደ ነዋሪዎች ምን አንደሚሰማን፣ ተከትሎም ለወደፊት እጣ ፈንታችን እንዴት እንደምናቅድ ጭምር ፖለቲካ የወሳኝነት ሚና ይጫወታል:: ሁለት አስርት ዓመታት አካባቢ ከቆየው የአንድ ፓርቲ አገዛዝ በኋላ ወደፊት አሻግረን የምንመለከተው ተጨማሪ የአንድን ፓርቲ አገዛዝ ዓመታትን እና ድምፁ የሚሰማው አባላቱ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባነሱት ቀልድ በሚስቁ ጊዜ የሆነውን «የይስሙላ» ፓርላማን ብቻ መሆኑ እድለቢስ ያደርገናል::

ዓመታት ባለፉ ቁጥር ኢህአዴግ እስካሁንም የበላይነቱን በማስጠበቅ ላይ ማተኮሩንና ይህንንም ከመካከለኛ አንስቶ ለረጅም ጊዜ ለማረጋገጥ የተቃዋሚ ፓርቲ እንቅስቃሴን በማዳከምም ጭምር ሁኔታዎችን ማመቻቸቱን መመልከት የሚያሳዝን፣ ተስፋ የሚያስቆርጥ ነው::

ከዓመታት በፊት በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የማስተርስ ፕሮግራም ላለመጀመር በወሰንኩኝ ጊዜ ያለ እውቀት ሁለተኛ ዲግሪ ሊሰጠኝ የሚችል ሥርዓት አካል መሆንን (በወቅቱ የነበረኝ የግል ስሜት በመቃወም እራሴን «አዋቂ» አድርጌ ቆጥሬ ነበር:: የማስተርስ ፕሮግራም ክፍያ «በክሬዲት አወር» ከ100 ብር ወደ 500 ብር ከፍ በተደረገ ጊዜ ትምህርቱን የማግኘት እድል በከፍተኛ ሁኔታ አደጋ ላይ በመውደቁ አዋቂነቴን ወደኋላ ዞሬ በመመልከት የተቆጨሁበት ሁኔታ ነበር:: እናም አሁን ማንም ሰው አቅም ኖሮትም ሊማር አይችልም:: ለኢትዮጵያ ታማኝ የሆነ ሰው በሽልማት መልክ ይሰጠዋል::

ተመራቂዎች እና አስቀድመው ሁለተኛ ዲግሪያቸውን የጀመሩት እድለኞች መሆናቸውን ደጋግመው ሲናገሩ ይደመጣል:: «አመለጥነው» ይላሉ:: አመለጥነው ሲሉ ከዚህ በኋላ በውጤት መሰረት ለቀጣይ ትምህርት ሁሉም ሰው ብቁ እድሉን የሚያገኝ ሊሆን የማይችልበትን የመንግስት ውሳኔ ማለታቸው ነው::

እናም የኢትዮጵያ መንግስት የመንግስትን እና የሀገሪቱን ጉዳዩች ከሚቆጣጠሩ የፖለቲካ ተሿሚዎች ጋር ወደ ሦስተኛው አስርት ዓመት አገዛዝ ይዘልቃሉ:: በዋነኛነት ከገዢው ፓርቲ ጋር የቀረበ ትብብር ያላቸውን የመንግስት ሰራተኞች ሲያስተምር የቆየው ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በመጀመሪያ አካባቢ ውጤት ያላመጡ ተማሪዎችን ለመጣል ይሳነው ነበር:: እነዚያ ተማሪዎች እዚያ የነበሩበትን ምክንያት በግልጽ ያውቁ ነበር፣ የማስወደቂያ ውጤቶችን ባገኙ ቁጥር «ኤፍ» እና «ዲ»ዎቻቸውን ወደ «ሲ» የሚያስቀይርላቸው ደብዳቤ አጽፈው ይመጡ ነበር:: ትምህርት እንዲቀስሙ ሳይሆን ዲግሪ እንዲይዙ ብቻ ነበር የሚፈለጉት:: አሁን የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓቱ «ታዋቂው» አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ጨምሮ በሁሉም የመንግስት ዩንቨርስቲዎች ተመሳሳይ ዓላማን ያስፈጽማል - ለተመሳሳይ ሰዎች ሁለተኛ እና ሦስተኛ ዲግሪዎችን መስጠት::

በዚህ ወቅት በመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ ያሉት የሥራ እድገት ለማግኘት የኢህአዴግ አባል መሆን እንዳለባቸው እንዲሰማቸው በመደረጉ ሳቢያ ጭንቀታቸውን

ይገልፃሉ:: የፓርቲ አባል ላልሆኑ ሰዎች የሥራ አስኪያጅነት ቦታዎች የማይታሰቡ ናቸው:: ለቀጣይ ጥቂት ዓመታት እንዲህ ላሉ ሰዎች ከፍተኛ ቦታዎችን መከልከል ቀላል ይሆናል፤ ምክንያቱም ፓርቲው በቂ የተማሩ አባላት ይኖሩታልና::

በጣም በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሁለት የሕዝብ መደቦች ይኖሩታል:- የኢህአዴግ የአመራሮች መደብ እና አጠቃላይ ህዝቡ:: ጆርጅ ኦርዌል «Animal Farm» መጽሀፉ ውስጥ «ሁሉም እንስሳት እኩል ናቸው፤ ነገር ግን አንዳንድ እንስሳት ከሌሎቹ የበለጠ እኩል ናቸው::» ብሎ ሲጽፍ ፀሀፊ ከመሆኑ ይበልጥ ነብይ እንደነበረ ምስክርነታችንን እየሰጠን ነው:: ለድህነታችን ሁሉንም ወቀሳ መሪዎቻችን ላይ ልናደርግ አለመቻላችን እውነት ነው:: የጥቂት ዓመታት መልካም ልማት በአንድ ዓመት ድርቅ ምክንያት ሙሉ ለሙሉ የወደመበትን አያሌ አስርት ዓመታትን ቆጥረናል:: አሁን ደግሞ ዓለም አቀፉ የገንዘብ ቀውስ እና የሀገር ውስጥ የኃይል እጥረት ተመሳሳዩን እየፈፀሙ ነው::
ኢኮኖሚው ያለበት የችግር መጠን አቶ ሴኩ ቱሬ ከሀገር ውስጥ ጋዜጣ ጋር ባደረጉት የቅርብ ጊዜ ቃለ ምልልስ ላይ በተዘዋዋሪ ተጠቁሞ ነበር::

ኢህአዴግ የመሬት አያያዝን በተለየ መልኩ ለማድረግ እያቀደ ነው፤ ነገር ግን አሁንም የህዝብ እና የመንግስት ንብረት መሆኑን ቀጥሎበታል:: ከእቅዶቹ አንዱ «ጂፒኤስ» መሰረት ባደረገ ሥርዓት የሁሉም የእርሻ መሬቶች አዲስ ምዝገባ ማካሄድ ነው:: አቶ ሴኩ በቃለ ምልልሳቸው ለዚህ ፕሮጀክት የሚያስፈልገው 90000 የአሜሪካ ዶላር በጣም ብዙ ስለሆነ ገዢው ፓርቲ ሊገኝ የሚችልበትን መንገዶች እያፈላለገ መሆኑን ገልፀዋል:: ያ ገንዘብ በ12 ብር ምንዛሪ ቢመታ ከአንድ ሚሊዮን ብር ጥቂት በያልፍ ነው:: እናም ይህ የገንዘብ መጠን የግብርና መር ኢንዱስትሪ ሀገሪቱ ልታወጣው የማትችለው መጠን የሆነበት ደረጃ ላይ ደርሰናል::

ዴሞክራሲ ምንድን ነው? ሁሉም ባለድርሻዎች እጣፈንታቸውን በመወሰኑ ረገድ ያገባኛል እንዲሉ እና እንዲሳተፉ የሚፈቅድ ሁኔታ አይደለምን? መሪዎች የዜጐችን እውቀት፣ ክህሎት እና አርበኛነት ለብሔራዊ ምክንያቶች ጥቅም ላይ ማዋልን አያመላክትም? ከህዝባዊ ዴሞክሲያዊ ሪፐብሊክ (ታስታወሱታላችሁ?)አንስቶ እስከ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ድረስ «ዴሞክራሲ» የሚለውን ቃል ብቻ ነው የምናውቀው::
ሆነም ቀረ (ዴሞክራሲን) ማንስ ይፈልገዋል? ካለእርሱስ ለረጅም ጊዜ ኖረንም የለ? በአንድ አካል የበላይነት ላይ የተመረኮዘ የራሳችንን (የዴሞክራሲ) ግልባጭ እየተገበርን በጮክታ ልናውጀው እንችላለን? የኢህአዴግ የ«እኛ» ዘመን የጀመረው ከአልባንያን ርዕዮተ ዓለም፣ እና ከሲንጋፖርያን የኢኮኖሚ ምኞት ጋር ነበር:: የመጀመሪያው ፍሬ ከርስኪ መሆን እና የሌላኛው ሊሳካ የማይችል መሆን፣ ብሎም ድጋፍ የሚሰጠን ምዕራቡ የመሆኑ እውነታ የእሳቤ ልዩነትን አመንጭቷል:: በሰብዓዊ መብቶች እና በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ተከታታይ ማስጠንቀቂያዎቻቸውን መቋቋም እስኪያቅተን ጊዜ ድረስ ምዕራቡን ወዳጅ እናደርጋለን:: በገጠር ልማት ላይ መሰረት ያደረገ መካከለኛ መደብ ኢኮኖሚ መገንባትን ማለማችን ቀጥሏል፤ የቻይና እና የሕንድ ሰፊ ምኞቶች

ከብድር፣ ከልገሳ እና ከኢንቨስትመንት ፍላጐቶቻችን ጋር ወደተስተካከለበት ወደ ምስራቅ አቅጣጫችንን ቀይረናል።

በፍጥነት እያደጉ ያሉት የእስያ ሀገራት አምሳያቸውን ለመተግበር ከባድ የሆኑ ሁለት ሞዴሎችን ያቀርባሉ። የቻይና ሀፍረት የለሽ አምባገነን ዴሞክራሲያዊ እሴቶች እና ኢኮኖሚያዊ ልማት እጅ ለእጅ ተያይዘው ይሄዳሉ የሚለውን እሳቤ በስኬታማ መልኩ ተቋቁሟል። ሁለቱን ሁኔታዎች ማካሄድ እጅግ ከባድ በመሆኑ ወደፊት ዴሞክራሲያዊ የመንግስት መዋቅር የመመስረት አቅም የለሽነቱ የተገነባውን ሁሉ የማፈራረሱ እውነታ ሊነጠል የማይችል ችግር ነው። የህንድ ሞዴል ይበልጥ ዘላቂ ተደርጐ የሚወሰድበት አንዱ ምክንያትም ያ ነው፤ የዚች ሀገር ኢካኖሚ በርግጥም በጥቂት አስርት ዓመታት ውስጥ የቻይናን እንደሚያልፍ ይጠበቃል። እኛ ጋርስ፣ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግስት ብለው አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግስት ብለው ሲጠሩት ኢትዮጵያን ወደ መካከለኛ ገቢ ሀገር የሚያሸጋግር ነው - ያም በወረቀት ላይ ነው።

በኢትዮጵያ የተሰራጨው ድህነት እጅግ ስር የሰደደ በመሆኑ የትኛውም ልማት ቢተገበር የሚታይ ውጤት ለማምጣት ጊዜ ይወስዳል። አሁን ባለው አሰራር ሀገሪቱ ካተረፈች የኢህአዴግን መደብ ልናመሰግነው ይገባል፤ ሀገሪቱ ካላተረፈች አሁንም የኢህአዴግ መደብ እናመሰግነዋለን፣ ምክንያቱም ችግሩን በብቁ ሁኔታ እንቆጣጠራለን ብለዋልና።

በአንድ ወቅት አንድ የቤተ ክርስቲያን ሰውን በቤተ ክርስቲያን ለሀገሪቱ፣ ቢያንስ ለኢኮኖሚያዊ ችግሮች የጾም እና የፀሎት ጊዜ እግዞታ እንደማይደረግ ጠይቄው ነበር። ምላሹ አስገርሞኛል። «እንዲያ ያለ የፀሎት ጊዜ እንዳይኖር መንግስት አዟል።» «ምናልክ!» «አዎ። እግዞታ ነገሮች ሁሉ ከቁጥጥር ውጪ ሲሆኑ የሚደረግ ፀሎት መሆኑን መንግስት ለቤተክርስትያኗ ተናግሯል ይባላል። መንግስት ሁሉንም ችግሮች በአግባቡ እየተመለከተ በመሆኑ ለህዝብ መረበሽ ምክንያት ለሚሆን እንዲህ ያለ ፀሎት ቦታ እንደሌለ ተገልጿል።» ህይወትን የማቆየት ዋጋው የጨመረበት ከባድ ችግር ተጋርጦብን በዝምታ መኖራችንን እንቀጥላለን።

ነገር ግን እኛን (አባቶቻችንንም ሆነ እናቶቻችንን) ድምፃችንን ከፍ አድርገን እንድንናገር ያበረታታን አልነበረም። ምናልባት ኢትዮጵያውያን ላለፉት 100 ዓመታት ድምፃቸውን ያሰሙት ስንት ጊዜ እንደሆነ አንድ ሰው ሊቆጥረው ይገባል። ክስተቶቹ ግን ብዙ አይባሉም።

# ምህረትና ምህሳ በፅኑ የሚያስፈልጋት አገር

**(Mercy Imperative Land)**

በመርዓዊ ሚጌሶ

ውድ አንባቢዬ፣ ለመሆኑ «መቅረዝ» የሚባል ነገር ያውቃሉ? አላወቁ ከሆነ እነሆ:- መቅረዝ በእንግሊዝኛ «Lamp Stand» ይባላል:: «Lamp Stand» ወይም መቅረዝ ማለት ብርሃን ተሸካሚ ዕቃ ወይም አቃፊ ማለት ነው:: መቅረዝ በተለይ ሻማ በማስቀመጫነቱ በስፋት ይታወቃል:: መቅረዝ ፍጥረታዊ ብረሃንን በመሸከሚያነት ከመገለፁ ባሻገር የዕውቀት ብርሃን ተሸካሚነት ምሳሌነትም አለው:: ለምሳሌ ት/ቤት የዕውቀት ብርሃን የሚተላለፍበት መድረክ ስለሆነ መቅረዝ ሊባል እንደሚቻል ማየት ይቻላል:: ጋዜጣ መቅረዝ ነው:: ሚዲያ መቅረዝ ነው:: መጽሐፍ መቅረዝ ነው:: የኤሌክትሪክ ምሰሶም መቅረዝ ነው:: የመብራት አቃፊዎችም መቅረዞች ናቸው:: ወዘተ . . . ::

አሁን ቁልፉ ጥያቄ መቅረዞቹስ አሉ፣ ግን ብርሃን አለባቸው ወይ? የሚለው ነው:: ለምሳሌ በቅርቡ የየመንገዱና የየቤቱ መቅረዞች ለወራቶች ብርሃን ተራ በተራ ሲለግሱን ቆይተዋል:: የነሱ ብዙ አሳሳቢ አይሆንም:: አሁን ችግሩ የአዕምሮ ብርሃን የሆነው ነገር መቅረዝ አግኝቷል ወይ? የሚለው ነው:: ይህን ጥያቄ ደግማችሁ ብታዩት፣ መቅረዞቹ አገር ለሚገነባበት ዕውቀት ክፍት ሆነዋል ወይ? እያልን ነው:: እናንተ እንዴት እንደምትረዱኝ ባላውቅም አፍሪቃ በዕወቀት ብርሃን መገንባት ስለሚገባው በበኩሌ በመቅረዜ ላይ ብርሃን እያበራሁ እንዳለሁ ነው የምረዳው:: ግን ታዲያ በዚህ የመረዳት ሂደት ልክ እንደሌሎቹ ብርሃን ተሸካሚ መቅረዞች የተቸገርኩበት ጉዳይ አለ:: ይኸውም ምንድነው፣ እኔ በግልጽ የምናገረውን አንዳንድ አንባቢ በራሱ መንገድ ገልብጦ የሚረዳኝ የመሆኑ ነገር ነው:: እንደ ፀሐይ ብርሃን በጠራ መልኩ የምገልፀውን ጉዳይ እንደቅኔ እየቆጠሩ የሚገነዘቡኝ ሰዎች ያናድዱኛል:: እንዳልኳችሁ እኔ ብቻ ሳልሆን ለምሳሌ ወንድሜ ሲራክም በዚሁ ጉዳይ አዝኖ ሲናገር ነበር ሰሞኑን:: እኛ የምንለውን እነሱ በራሳቸው መንገድ እየተረዱ ተቸግሬያለሁ በሚል ብሶቱን መሸሸግ አቅቶት ሲናገር ነበር - ሲራክም::

ለምሳሌ ባለፈው ሳምንት «የስሙ-ነጋ አገር መሆናችን ነወይ?» በሚል ዓይነት ግልጽ ነገር ጽፌ እህት ራሄል እንኳ «ሰለዘር ነው የፃፍከው» ብላ አስገርማኛለች:: ስለዘር ስትይ:- «ስለመዝራትና ማጭድ ማለትሽ ነው ወይ?» ብዬ ግራ በመጋባት ጠይቄያት ፈገግ እያለች፣ «አይ....» አለች:: አስፈላጊ ከሆነ ከጠቃሚነቱ አንጻር በተጠቀሰው ጉዳይ ላይም እጽፋለሁ:: እኔ ስለእውቀትና ጥበብ ማዕዘናት እንጂ ተራ ሽሙጥ፣ አሉባልታና አሽሙር ፀሐፊ አይደለሁም:: ወይም ደግሞ በእብራይስጥ፣ ሮማይስጥ ወይም ግሪክ ወይም ግዕዝ ቋንቋ እየተናገርን ስላይደለ በጠራ አዕምሮ ልንናበብ ይገባል:: ወይም ደግሞ ፊዚክስ ወይም ካልኩለስ አንጽፍም:: ቀላል፣ ግልጽ ግን መሰረታዊ ነገር እንጽፋለን:: ለማንኛውም ስለመቅረዝና አገልግሎቱ ሰፋ ያለ ርዕስ በሌላ ጊዜ ለማቅረብ መትጋቴን እየጠቆምኩ፣ ወደዛሬው ርዕሰ ጉዳይ እመለሳለሁ::

እንደሚታወቀው እነ ቮልቴርና አርስቶትል፣ ካርል ማርክስና ፕሌቶ፣ እነ ፍራንሲስ ቤከን ወይም ኦስካር ዋይልድ፣ ዊልያም ሼክስፒር ወይም ፍሬድሪክ ኤንግልስ እና አልበርት አንስታይን . . . በመረጃነት እየተጠቀሱ ሲፃፍ፣ ሲነበብ፣ ሲደሰኩርና ሲነበነብ ማንነታችንን የኩራት ማማ ላይ እንሰቀላለን:: «አባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል» እንዲሉ እነዚህንና መሰሎቻቸውን የፈጠረውንና በየዘመናቱም አንዳንድ መገለጦችን በመስጠት ወይም በተቃዋሚነት እንዲሰለፉ በመፍቀድ ለአንዳንድ ዘመን የላካቸውን መድኃኒዓለምን ግን እንቃወማለን፣ አልፎ ተርፎም ከዚህ ዋና ምንጭና መገኛ መስማት እንኳን አንፈልግም የሚሉ መኖራቸው አስገራሚ ነገር ሆኗል:: «ሁሉ በሁሉ» የሆነ አምላክ በስነ-ጥበቡ ራሱን በሼክስፒር ቢገልጥ፣ በፊዚክሱ ደግሞ በአልበርት አንስታይን ራሱን መግለጡን ማየት ስላቃተን የፈጣሪ ስም ሲጠራ አጋንንት እንደተጠናወተው መፃጉ ያንቀጠቅጠናል:: ርግጥ ነው፣ ስመ እግዚአብሔር አጋንንት ላለባቸውና ይህንኑም ለማይረዱ የባላጋራ ስም ያህል አንቀጥቃጭ ስም ነው:: በተቻላቸው መጠንም ይህን ጌታ ሊዋጉት ይታገላሉ ግን ሲታገሉት ይወድቃሉ፣ ይደቅቃሉም::

የእያንዳንዱ ገንቢ ስነ-ጥበብ ባለቤት ፈጣሪ አምላክ ቢሆንም ደመናውን ከፀሀይ አቅም ውጭ እንደተደራጀ የሚቆጥሩ ዕውሮች የፈጣሪ አምላክን የሥልጣኔ ባለቤትነት ሚና ይክዳሉ:: በባህሩ ላይ ሙቀቷን በመልቀቅ የሳበችውን ነጠብጣብ (ትነት) ደመና አድርጋ በመቋጠር ያደራጀችውን የፀሀይ ሚና የመካድ ያህል ከማናቸውም ገንቢ ሥልጣኔ በስተጀርባ ያለውን የልዑል አምላክ እግዚአብሔር ሚናን የማይመለከቱ ዛሬ ዛሬ ጥቂቶች አይደሉም:: ፈጣሪ አምላክ ሃይማኖት ከተባለው ጉዳይ በላይ መሆኑን ያላስተዋሉ (የሃይማኖት መሪዎቹንም ሊጨምር ይችላል) ጥቂቶች አይደሉም:: ጠቢባን ነን የሚሉ ነገር ግን ንጉስ ሰለሞንን ከጥበቡ ጌታ ለይተው የሚመለከቱ ጥቂቶች አይደሉም:: ዝነኛውን ከአሰልጣኙ ለይቶ ከማየት የከፋ ዕውርነት እንጠበቅ እንጂ የነገሩን ሁሉ ባለቤት ችላ ማለታችን እጅግ አሳዛኝና አስተዛዛቢ ነው::

ዛሬ ለማለት የተፈለገው ባጭሩ ከማንኛውም ልማት ወይም ሥልጣኔ በስተጀርባ ፈጣሪ አምላክ አለ፣ ከማንኛውም ውድቀት በስተጀርባም የዚሁ የፈጣሪ አምላክ ቁጣ (ቅጣት!) አለ የሚለው ሆኖ፣ አገራችን ካለችበት መለኮታዊ ቁጣ ትድን ዘንድ ወደ ምህረት ሰጪውና አቅጣጫ አመልካቹ መድኃኒዓለም (ይህም በኦሮሚያ ዋቃ፣ በአረቢኛ አላህ፣ በእንግሊዝኛ «God») በፀሎትና በምልጃ በፊቱ እንቅረብ የሚል መልዕክት ማስተላለፍ ነው:: በዓለም ላይ አንድ ብቸኛ አምላክ ነውና ያለው ወደዚህ ጌታ እንቅረብና በአባቶቻችንና በእኛም በልጆቻቸው ላይ ከተፈራረቁብን የዘመናት ቁጣ እንዳን! ለዚህም በመንደርደሪያነት ወይም በመረጃነት ከዚህ የዘመናት መለኮታዊ ቃል በመጥቀስ እንጀምር ብለናል፦

አራት ሰዎች የተሸከሙትን ሽባ አመጡለት:: ስለህዝቡም ብዛት ወደእርሱ ማቅረብ ቢያቅታቸው እርሱ ያለበትን የቤቱን ጣሪያ አነሱ (Desperate Search ቢባል)

ነድለውም ሽባው የተኛበትን አልጋ አወረዱ:: ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን:- አንተ ልጅ ኃጢዓትህ ተሰርየችልህ አለው:: ከጻፎችም አንዳንዶች በዚያ ተቀምጠው ነበር - በልባቸውም ይህ ሰው ስለምን እንደዚህ ያለ ስድብ (blasphemy) ይናገራል? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ኃጢዓት ሊያስተሰርይ ማን ይችላል? ብለው አሰቡ:: ወዲያውም እየሱስ በልባቸው እንዲህ እንዳሰቡ በመንፈሱ አውቆ እንዲህ አላቸው:- በልባችሁ ይህን ስለምን ታስባላችሁ? ሽባውን ኃጢዓትህ ተሰርየችልህ ከማለት ወይስ ተነሳ አልጋህንም ተሸከምና ሂድ ከማለት ማናቸው ይቀላል? ነገር ግን ለሰው ልጅ በምድር ላይ ኃጢዓትን ሊያስተሰርይ ሥልጣን እንዳለው እንድታወቁ፣ ሽባውን አንተን እልሃለሁ ተነሳ አልጋህን ተሸከምና ወደቤትህ ሂድ አለው:: ተነስቶም ወዲያው አልጋውን ተሸክሞ በሁሉ ፊት ወጣ:: ስለዚህም ሠዎች ሁሉ ተገረሙና እንዲህ ያለ ከቶ አላየንም ብለው እግዚአብሔርን አከበሩ:: (ማር :2:1-12)

ኢትዮጵያ በተለያዩ ችግሮች ያለፈችና እያለፈች ያለ ሲሆን በየዘመኑ መፍትሔ ለማቀበል የሚተጉ ሰዎችንም ያስተናገደች ይመስለኛል:: ከነዚህም መካከል እነ ጳውሎስ ኞኞን የመሳሰሉ በቅርብ የመፍትሔው አካል ለመሆን አንደተንቀሳቀሱ የዚህኑ ሰው ሥራ በመቃኘት መረዳት ይቻላል:: ይህ ሰው በአንድ ወቅት ቅድስት ማርያምን ስለሚያከብርበት ምክንያት ተጠይቆ (ጥያቄውን ዘንግቼዋለሁ)፣ «ከግንድ የሚያላጋ ልጅ አላት» ማለቱ ትዝ ይለኛል:: «ታላቅና ኃያል ነው» ለማለት በመፈለግ:- ከግንድ የሚያላጋ ልጅ በማለት ስለክርስቶስ ገለጸ እንጂ፣ ጳውሎስ ክርስቶስ እንደ ሁኔታው ስብ መጋቢ (መፍትሔ ሰጪ) አምላክ መሆኑንም ያስተውላል::

ክርስቶስ ወደዚህ ምደር የመጣው በኃጢዓት ምክንያት ከክብር የጎደለውን የሰው ልጅ ለጊዜውም ሆነ ለዘለዓለም ለማዳን ነው:: ስለዚህ ክርስቶስ መጣ ማለት መፍትሔ መጣ ማለት ነው::

ወንጌላትን ለተመለከተ አስተዋይ ሰው ክርስቶስ በረገጠበት ሥፍራ መፍትሔ ረገጠ የማለትን ያህል ትክክል ነው:: በየደረሰበት የዕወራንን ዓይኖች ከፍቷል፣ ሽባዎችን ተርትሯል፣ የልብ ስብራትን ጠግኗል፣ የተራቡን መግቧል፣ ትዕቢተኞችን አዋርዷል፣ ትሁታንን ከፍ አድርጓል፣ ለሙታን ሕይወት ሰጥቷል . . .

ክርስቶስ ወደዚህ ምደር በድንግል ተወልዶ ከተመላለሰና ስራ ከጀመረ አንስቶ በአደራረጉ በየስፍራው በአብዛኛው ሶስት ዋና ገፀ-ባህሪያት ፍንትው ብለው ታይተዋል፤ (1) መፍትሔ ፈላጊው ሰፊ ህዝብ፣ (2) ምሁር ነኝ ባዩ ፈሪሳዊና ፃፊ፣ እንደዚሁም (3) መፍትሔ ሰጪው ክርስቶስ ራሱ ናቸው:: ወንጌላትን ሳታነቡ እነዚህን ካስተዋላችሁ ወንጌልን በቀላሉ መረዳት የሚቻል ይመስለኛል::

የክርስቶስ ሥራ እንዳይኖር ዕንቅፋት የነበሩትና በመጨረሻውም ስቅላቱን ያቀነባበሩ መሰሪ ተቃዋሚዎቹ ፈርሳውያንና ፃፎች እንደዚሁም የካህናት አለቆች ነበሩ:: እነዚህ ተቃዋሚዎች ለዘመናት ከምዕመናቸው ሙገሳ ለምደው ገዥ እውቀት አለን

በማለት ሲኩራራና ክብረ እግዚአብሔርን ሲዘርፍ የኖረ ስብዕና የነበራቸው ስለነበረ በድንገት ሰው የሆነ አምላክ ካልተጠበቀ ስፍራ መጥቶ ተጎጂውን ህዝብ በመፍትሔ ሲያጠግበው አጃቢያቸውና አሽርጋጃቸው ስለከዳቸው በጥቅም፣ በከንቱ ውዳሴ ታውረው መፍትሔውን በግልጽ በመካድ ለክብራቸው ገዶአቸው በተቃዋሚ ጎራ ፀንተው ቆሙ።

ካሉበት የወረዳ ደረጃ የላቀና የመጠቀ ብቃት ይዞ ሥርዓታቸውን አራቁቶ ሲያፈራርስባቸው ጌታቸውን ለመስቀል ተግተው በመለኮት ዓላማ ምክንያት ተከናውኖላቸው ነበረ። ያም ሆኖ ግን ከሞት በላይ ኃያል ሆኖ ያተሙትን መቃብር ፈንቅሎ ስላሳፈራቸው ለዘለዓለም ውርደት ተለይተው መወሰናቸውን እውን አደረጉ።

ጌታ ክርስቶስ በዚህ የምድር አገልግሎቱ ለበርካታ ጉዳዮች መፍትሔ የሰጠ ሆኖ በአንድ ወቅት ግን ለዛሬው ርዕስ መነሻ የሆነውን መፍትሔ ሰጥቷል።

ሰውየው ሽባ (Paralytic) ሆኖ ለብዙ ጊዜ መፍትሄ ጠፍቶ እሱም ቤተሰቡም (በእርሱ ላይ ኃላፊነት ያለባቸው) የመፍትሔ ያለህ! በማለት ተቸግረው ነበር። ብዙ የመፍትሔ ፍለጋ ተደረገ፤ መፍትሄ ግን አልተገኘም። አንድ ቀን ግን፣ አዎ አንድ ቀን አንድ ነገር ተሰማ። ክርስቶስ ጌታ፣ ሽባንም ይተረትራል የሚል ዜና ተሰማ - ያን ቀን። ሽባነቱ ያሰቃየው ተጎጂና ቤተሰቡም ወደዚህ የመፍትሔ ቦታ እንሂድ ሲሉ ተነሱ። አልጋው ላይ ያለውን ሽባም 4 ሆነው በመሸከም ወደ አየሱስ አመጡት። መፍትሔ ፈላጊዎች መውጪያና መግቢያ ዘግተው ሊያስገቡት ስላልተቻላቸው ኢየሱስ የተቀመጠበትን ቤት ጣሪያ ለማንሳት ስለተገደዱ ጣሪያውን ነደሉ፤ ሽባውንም ከጣሪያ ኢየሱስ ወዳለበት ቁልቁል አወረዱት። የፈለገ ዋጋ ይከፈል ሽባው በኢየሱስ መታየትና መፈወስ አለበት ብለው መወሰናቸውም ኢየሱስን አስገረመው። ሌላ አገልግሎቱን በማቋረጥም ይኼንን ድንገተኛ (ጣልቃ ገብ) ጉዳይ ማየቱን መረጠ። ዛሬም ይኼው ነው አሰራሩ። መፍትሔ ለማግኘት ምንም ዋጋ ያስከፍል (At any cost) ማንን እንመርጣለን? ይኼ በእግዚአብሔር የሚታይ መሰረታዊ ጉዳይ ነው።

ከዚያስ፣ ከዚያማ ወደ መፍትሔ መስጠቱ አልፎ ሽባውን አስቀድሞ ምን አለው? አዎ፣ «ኃጢዓትህ ተሰርየችልህ!» አለው። ይኼ አባባል ግን ፈሪሳውያኑን አስቆጣ። ላይ ላዩን አይተው (በ «Face Value») ለሚፈርዱ ፈሪሳዊያን አባባሉ አስቆጪ ሆኖ ተገኘ። ይሄ ሥልጣን የእግዚአብሔር እንጅ የዚህ ገሊላዊ አይደለም በሚል ነው የተቆጡት። እናያለን ባዮች ናቸው፤ ነገር ግን አምላክ ሰው ሆኖ መምጣቱን አላስተዋሉም። ይኼ ሳያንስ ደግሞ ቀጠለና «ተነሳ አልጋህንም ተሸክመህ ሂድ!» በማለት ሲናገር፣ ከአልጋው ተነስቶ ለዓመታት የተሸከመውን አልጋ ተሸክሞ በጉባኤው መካከል እያዩት ወጣ! ይህም የፈሪሣውያኑን አፍ አዘጋ።

ስለናንተ አላውቅም፣ በበኩሌ የኢትዮጵያም ሁኔታ በዚሁ ዓይነትም ታይቶኛል። ኢትዮጵያ ለዘመናት ስትረዳ በአልጋ ላይ የኖረች አገር ነች። ብድር፣ ዕርዳታ፣ ልገሳ ስትቀበል ለዘመናት በአልጋ ላይ ኖራለች። በዚህ ምክንያት ካለችበት ሁኔታ ሊያወጧት ባለመቻላቸው መሪዎቿም ግራ ተጋብተዋል። ምን ጉድ ነው ብንላት፣ ብንሰራት እቺ አገር ካለችበት አትንቀሳቀስም እንዴ? ብለዋል ማለት ይቻላል። ይኼ ሁኔታ በምዕተ

ዓመታት የሚቆጠር የአገሪቱ ገጽታ ነው፡፡ በበኩሌ ነገሥታት ይመኑም አይመኑም ነገሥታት በእግዚአብሔር እንዲሾሙ ስለማምን ማንኛውም መሪ ኢትዮጵያ ከወጣችበት አልጋ እንዳትወርድ ይሰራል ብዬ ማመን አልፈልግም፡፡ እንዲያውም በዚሁ ጋዜጣ በአንድ መልዕክቴ ላይ እንዳመለከትኩት ማንኛውም የፖለቲካ አስተዳደር የመለኮት ውሳኔን አስፈፃሚ ስለሆነ አንድን ነገር ከአልጋ ወርደሽ አልጋሽን ተሸክመሽ ሂጂ ማለት ወይም በአልጋ ማቆየት የሱ (የባለስልጣኑ) ውሳኔ አይደለም፡፡

በዚህ ታሪካዊ የመገለጥ ጊዜ ግን መሪዎቹ ኢትዮጵያን ከነአልጋዋ (ከወደቀችበት የተጠላለፈ የዘመናት ችግር ጋር) ወደ ክርስቶስ የማምጣት ሥራ መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህም ማንኛውንም ዋጋ መክፈል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ንጉስ በመቅረቡ ተቃዋሚዎች - ሀሳቡን የሚቃወሙ - ሊሳለቁ ቢችሉም መፍትሔ ሰጪውን ከመጠበቅ ሌላ ያለ አተካሮ አስፈላጊ አይሆንም፡፡

ኢትዮጵያ ከወደቀችበት የእዳ፣ የበሽታ፣ የብድር፣ የጉስቁልና ... «አልጋ» የምትወርድበት ጊዜ አሁን ነው፡፡ ይህን መገለጥ ቸል ብንል አገሪቱ መዳን ከሌላ ስፍራ ይሆንላታል፣ አደራ ተቀባዮቹ ግን ከጌታ ፍርድ በታች ልትሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ ምርጫችሁን አስተካክሉ፡፡

ከመቼውም ጊዜ በላይ የምህረትና የምህላ ጊዜ ለአገሪቱ የሚያስፈልገው አሁን ነው፡፡ ጉዳዩን እጅግ ጠቢብ ወደሆነው አምላክ ማቅረብ ጠቢብነት እንጂ ድንቁርና አይደለም፡፡ በምንም ሀይማኖት ራስህን ደልድል፣ ወደ ጠቢቡ አምላክ የቀረበ ጉዳዩ በሀፍረት አይመለስም፡፡ ወደ እርሱ ሽባ ሆኖ ሄዶ ኮራ ብሎ እየተዝናኑ መውጣት ግድ ነው፡፡ መጽሐፉ በየዘርፉ የመፍትሔ ቀመር የታጨቀበት መጽሐፍ በመሆኑ ልንጠራጠረው አይገባም፡፡ የአገሪቱ የፈውስ ሥርዓት (System) እንዴት እንደሚታረም ወደሚያሳውቀው ጌታ ጉዳዩ ሳይውል ሳያድር ይቅረብ፡፡ በዚህም አገሪቱን ሽባ ያደረገው በደል ይወገድ፤ ለጥቆም አገሪቱ በሁለት እግሯ ትራመድ፡፡

ይህ የወንጌል ቃል ትርጓሜው አንድ ዓይነት ሲሆን ልዩ ልዩ ትግበራ (application) ስላለው፣ ደሞ ወንጌል ባገር ጉዳይ ምን አገባው? በሚል ባላጋራው እንዳይሸነግላችሁ ለቃሉ ታዘዙ፡፡ ይኼ ዘለዓለማዊ ቃል አንባቢዎቼ ላለባቸው የግል ጉዳይም ፋይዳው ያው ነው፡- በአልጋ ላይ ለተኛባችሁ ሽባ ጉዳያችሁ ሁሉ ፈውስን በመፍትሔነት የሚያመጣ ነውና ታዘዙት፡፡

ባጠቃላይ እንግዲህ፣ ኢትዮጵያ ተፈወሳ እንያት! በአገር ጉዳይ አልጋውን ከ4 ወገን የሚይዙት እነማን ናቸው የሚለውን ባጭሩ አይተን እንጠቃለል፡፡ እኔ እንዳየሁት ሕግ አውጭው፣ ሕግ አስፈፃሚውና ሕግ ተርጓሚው ሶስቱን እግር ሲይዙ ተቃዋሚው 4ኛውን እግር በመያዝ ጉዳዩን በመፍትሔ ሰጪነት ምናልባትም በህልማችሁ እንኳ ወዳላያችሁት ጌታ አቅርቡት፡፡

ሰላም ሁኑልኝ! ደህና ቆዩን፡፡

# ሲበራሊዝም፣ የሕግ የበላይነት እና ነፃ ገበያ

በግዛው ለገሰ

**«የሕግ የበላይነት ሲተገበርና ሲከበር፣ የሰው ልጅ የመፍጠር እምቅ ኃይሎች ነፃ ይወጣሉ፡፡»**

ፕሮፌሰር ሪቻርድ ኤብሊንግ

ከታሪክ አንፃር ሊበራሊዝም የግለሰባዊ ነፃነት (Individual Liberty) የፖለቲካ ፍልስፍና ነው፡፡ አንድ ግለሰብ የፈቀደውን ለማሰብ፣ ለመናገርና ለመፃፍ፤ የፈቀደውን ለማመን እና ለማምለክ፤ እንዲሁም እንዳሻው ህይወቱን በሰላማዊ መንገድ ለመኖር ነፃ ሊሆን እንደሚገባ ሊበራሊዝም ያውጃል፡፡

ሪቻርጅ አም. ኤብሊንግ የኢኮኖሚክስ ፕሮፌሰር ናቸው - በሂልስዴል፣ ሚቺጋን ሂልስዴል ኮሌጅ፡፡ በአሁኑ ሰዓት «The Foundation for Economics Education-FEE» የተባለውን ተቋም በፕሬዝዳንትነት ይመራሉ፡፡ ፕሮፌሰር ኤብሊነግ «Free Markets, the Rule of Law, and Classic Liberalism» በተሰኘ ጽሁፋቸው የሰው ልጅን ተፈጥሯዊ ነፃነት፣ የነፃ ገበያን አፈጣጠር እና የእነዚህንም በሕግ የላይነት መከበር በስፋት ይተነትናሉ፡፡ የዛሬ ጽሁፋችን በዚህ የፕሮፌሰር ሪቻርድ ኤብሊንግ ትንተና ላይ ይመረኮዛል፡፡

ፕሮፌሰሩ በጽሁፋቸው የሊበራሊዝም ፍልስፍና እጅግ ጥበበኛና ከሁሉም የላቁ ሰዎች እንኳን ሟቾች መሆናቸውን እንደሚያሰፍር ይጠቁማሉ፡፡ እጅግ ጥበበኛና ከሁሉም የላቁ ሰዎችም ቢሆኑ የፈጣሪ ብቻ የሆነው ፍፁም ዕውቀት፣ በሁሉም ቦታ የመገኘት እና ሁሉን የማድረግ ችሎታ ይጉድላቸዋል፡፡ ሰዎች ፍፁም ባልሆነው የእውቀታቸው ንፍቀ ክበብ ወስጥ ያለውን ዓለም የሚመለከቱት እና የሚገነዘቡት ከራሳቸው ጠባብ እይታ አንፃር እና ከፈጣሪ ጋር ሲነፃፀር እጅግ ውስን በሆነ አዕምሮአዊ እና አካላዊ ኃይል መሆኑን ፕሮፌሰሩ ያስታውሳሉ፡፡

በዚህም የተነሳ ማንም ሰው ያለውን የሰውን እና የዓለምን ሙሉ ግንዛቤ ከፈጣሪ ጋር ሊያስተካክል እንደማይቻለው በመግለጽ «ማንም ሰው የማንኛውንም ሌላ ሰው ለግዙፍ እና ወሳኝ ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት ህሊናን የመከተል ነፃነት ለመንፈግ አይችልም፡፡» ይላሉ ጸሀፊው፡፡ ይህ የሰው ልጅ ህሊናውን የመከተል ነፃነቱ ለህልውናው ጭምር እጅግ ወሳኝ በመሆኑ ፖለቲካዊ ቁጥጥር ሊደረግበት እንደማይገባም ይገልፃሉ፡፡

«የፖለቲካ ቁጥጥር በመሰረታዊ መልኩ የአካላዊ ኃይል ሥልጣን ነው፡፡ የማስገደድ ሁኔታ ይመጣል በሚል ስጋት ከዜጐች አንድን ነገር ለማድረግ ወይም

ላለማድረግ እሺታን የመጠየቅ መብት ነው፡፡» ይላሉ ኤብሊንግ፡፡ የፖለቲካ ሥልጣን ህዝቦች በምን መልኩ መኖር፣ ማሰብ እና መራመድ እንዳለባቸው ለማስገደድ ጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችል በመግለጽ፣ «በአካላዊ ጉዳት ስጋት ምክንያት አንድ ሰው የሌላን ሰው ፍላጐት እርሱ ወደፈቀደው መልኩ መጠምዘዝ ነው፡፡» ይላሉ፡፡

«በህሊናው በመመራቱ ምክንያት ማንም ሰው ሊሰቃይ (torture) ወይም ለሞት ሊዳረግ አይገባም፡፡» የሚለው የሊበራሊዝም ፍልስፍና እንደሆነ ኤብሊንግ ይናገራሉ፡፡ «ከዚህም በላይ የፖለቲካ ሥልጣን ሰዎች ምን ማመን እንደሚገባቸውና እንዴት በሰላማዊ መንገድ መራመድ እንዳለባቸው ለማስተማር (ለመጠቀም) ጥቅም ላይ ከዋለ እነዚያ የሚጋጩ እምነቶች፣ አመለካከቶች እና ሀሳቦች ያሏቸው ሁሉ የፖለቲካ ሥልጣንን ለመቆጣጠር ትንቅንቅ ስለሚገጥሙ ህብረተሰቡ ማቆሚያ የሌለው ትግል ይጋረጥበታል፡፡ የየትኞቹ ወገኖች የመልካም፣ የውብ፣ የትክክል፣ እና የፍትሃዊነት ግንዛቤዎች ሁሉም ህብረተሰብ ላይ ተግባራዊ እንደሚሆኑ ለመወሰን የሞት ሽረት ትግሉ ይቀጥላል፡፡ በዚህ ዓይነት ትግል እና ትንቅንቅ ሳቢያ የሰዎች ዓለም የሰው ልጆች ህይወት መጥፋት እና የቁሶች ውድመት የሚታይበት ምድራዊ ገሃነም ይሆናል፡፡»

ሪቻርድ ኤብሊንግ ከላይ ባለው አንቀጽ የገለፁት ሂደት የሰው ልጅ እስከ አሁኗ ሰዓት ድረስ እንዴት መኖር ሊቀጥል እንደቻለ፣ ብሎም ሁልጊዜም ባይሆን የምንተነፍሰው የሰላም አየር እንዴት እንዳልጠፋ ጥያቄ ያጭራል፡፡ ይሁንና ግን እራሳቸው ምላሹን ያስቀምጣሉ - መቻቻል (tolerance)፡፡ «ሁሉም ሰው የሌሎችን ሰዎች በህሊናቸው ትዕዛዝ የመመራት መብት ሊያከብር ይገባል፡፡»

የፖለቲካ ሥልጣን ወይም መንግስት የማሰብ ነፃነት እና ሌሎች የግል ነፃነቶች የሆኑትን እንዳይገረስስ እንዴት መከልከል ይቻላል? የፖለቲካ ሥልጣን ያላቸው ሰዎች የሌሎችን ሰዎች መብቶች እንዳይነኩ እንዴት መገደብ ይቻላል? ፕሮፌሰር ሪቻርድ ኤብሊንግ «ሕጉ ሊደነገግ የቻለበት ዓላማ ምንም ይሁን፣ ሁሉም ሕግ ሰው-ሰራሽ ነው፡፡» ይላሉ፡፡ «ሕጉን የቀመሩትም ሆነ የተስማሙበት፣ ለመከበሩና ለመፈፀሙ ሥነ-ሥርዓትን የመሰረቱትም ሆነ የሚያስፈጽሙት ሰዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ የሰው ልጅ ከሕግ እና ከሕግ ሂደት መቼም ቢሆን አይለያይም፡፡» ታዲያ የሰዎች የበለይነትን እና የሕግ የበላይነትን በምን መለየት ይቻላል?

«ህብረተሰቡ በሰዎች የበላይነት ስር ሳይሆን በሕግ የበላይነት ስር መኖሩን የማስጠበቂያው መንገድ እነኝያ ሕጉን የሚያስፈጽሙት እንኳን ሳይቀሩ ከተቀረው ዜጋ ጋር ባላቸው ግንኙነቶች በግልጽ በተቀመጡ ሥነ-ሥርዓቶች ተጠያቂ እንዲሆኑ የሚያደርገው ነው፡፡» ሲሉ የሕግ የበላይነትን ሚና ይጠቅሳሉ፡፡ እንግሊዛዊው የሕግ ፈላስፋ አልበርት ቬን ዳይሴይ በ19ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ አካባቢ እንደገለጸው፣ «... ከጠቅላይ ሚኒስትሩ እስከ ታች ኮንስታብል አልያም ግብር ሰብሳቢው ድረስ እንደማንኛ ውም ሌላ ዜጋ አለሕግ ማረጋገጫ ለሚፈጽሙት ተግባር በተመሳሳይ ሁኔታ ተጠያቂዎች ናቸው፡፡»

በሕግ የበላይነት ውስጥ የሚካተተው አንዱ መሰረታዊ ንጥረ ነገር መንግስት በዜጎች ላይ ማድረግ የሌለበትን ማስቀመጡ ነው:: ጸሀፊው የዜጎችን አላግባብ መያዝን (መታሰርን) እንደምሳሌ ያነሳሉ:: «መንግስትም ሆነ የተለያዩ ሕጋዊ ወኪሎቹ አንድን ግለሰብ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ፍርድ ቤት ቀርቦ ክስ ሳይመሰረትበት አስሮ ሊያቆዩት አይችሉም::» ይላሉ:: አካልን ነፃ የማውጣት ሂደት (habeas corpus) ማንም ሰው በሕግ ክስ ሳይመሰረትበት ተይዞ ሊቆይ እንደማይገባ ያረጋግጣል:: እናም ግለሰቡ ፍርደ ቤት ቀርቦ የሕግ ጥሰትና ሰውየውን ለመያዝ የሚያስችል በቂ ምክንያት ስለመኖሩ ማሳየት ካልተቻለ ከእስር ሊፈታ ይገባል:: «የሕግ የበላይነት ልዩ የሆነው ብቃቱ የፖለቲካ ሥርዓቱን በሚቆጣጠሩት እጅ ያለውን አግባብ የለሽ ሥልጣን ሙለ ለሙሉ ባያስወግድም ለመቀነስ መሞከሩ ነው::»

ፕሮፌሰሩ ርዕሰ ጉዳያቸውን የበለጠ ለማብራራት የመንገድ ሕጎችን እንደምሳሌ በማንሳት ሊበራሊዝም በመቻቻል እና በሕግ የበላይነት እንዴት እንደሚደገፍ ያሳያሉ:: የመንገድ ሕጎች መኪኖች በመንገዱ በቀኝ በኩል አልያም በግራ በኩል እንደሚጓዙ፣ ቀይ መብራት ሲበራ ሁሉም መኪኖች ቆመው እንደሚጠብቁና አረንጓዴ ሲበራም መንቀሳቀስ እንደሚችሉ፤ የተገለፁ የፍጥነት መጠኖች መከበር እንደሚገባቸው፤ እንዲሁም የፖሊስ መኪና ወይም አምቡላንስ ሲመጣ ሁሉም መኪኖች መንገድ መልቀቅ እንዳለባቸው ይደነግጋሉ::

እነዚህ የመንገድ ሕጎች ጥቅል እና የማይለዋወጡ በመሆናቸው በሁሉም አሽከርካሪዎች ላይ በእኩል መልኩ ከመስራታቸው አልፎ ለማንም ሰው ልዩ መብት አይሰጡም፣ ማንም ሰው ላይ የተለየ ግዴታ አይጭኑም:: ከዚህም በላይ እያንዳንዱ አሽከርካሪ እነኚህን ሕጎች እስከተከተለ ድረስ በፈቀደው ጊዜና ለፈቀደው ዓላማ በመንገዶቹ ላይ ለመጓዝ ነፃነት አለው:: እናም ህዝቡ የመንገድ ሕጎቹን የሚከተልበት ዓላማ አስፈላጊ አይደለም:: «በሕግ የበላይነት ስር ያለ የአንድ ነፃ ህብረተሰብ ዋነኛው መለያ ህብረተሰቡ ራሱ እንዲፈጽም የሚጠበቅበት ዓላማ፣ ወይም «የተገለጠ እጣፈንታ» ወይም «ታሪካዊ ሚና» የለውም:: ነፃ ህብረተሰብ ከግለሰብ እቅዶች እና ዓላማዎች የተነጠሉ እቅዶች ወይም ዓላማዎች የሉትም::» ይላሉ ሪቻርድ ኤብሊንግ::

«ክላሲካል» ሊበራሊዝም በግለሰብ ነፃነት እና የግል ንብረት የመያዝ መብት መካከል ላለው ትስስርም አጽንኦት እንደሚሰጥ ጸሀፊው ይገልፃሉ:: የሁለቱን ትስስርም በከፊል በፍትህ እሳቤ ላይ መሰረት ያደረገ እንደሆነ በማስረዳት፣ «አንድ ሰው በንፁህነት እና በሰላማዊ መንገድ በጥረቶቹ ያመረተው፣ ወይም ከሌሎች ጋር ባደረገው በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ልውውጥ ያገኘው ንብረት የራሱ እንደሆነ ሊቆጠርለት ይገባል::» ይላሉ:: የግል ንብረት ጉዳይ ለሌሎች ጥቅም በማመንጨት (Utilitarian efficiency) በኩልም ይገለፃል፣ «ሰዎች ከራሳቸው ከሆነ ነገር በሚፈልቅ ሥራ ክፍያ እንደሚያገኙ ሲያውቁ ኢንዱስትሪያቸውን በአምራች እና ፈጠራ በተሞላበት መንገድ ለመተግበር ተነሳሽነቱ እና ማበረታቸው ይኖራቸዋል::»

በሌላ በኩል ሊበራሊዝም ለግል ንብረት ቦታ የሚሰጥበት ምክንያት ግለሰቡን ከፖለቲካ የሥልጣን አላግባብ አተገባበር ሊያድነው የሚችል አቅም ሊያቀርብ በመቻሉ ነው:: የግል ንብረት ለግለሰቡ ከፖለቲካ ኃይል ቁጥጥር ነፃ በሆነ መልኩ የራሱን ህይወት ሊነድፍ እና ሊቀርጽ የሚያስችለውን እድል ይሰጠዋል:: «በራሱ ጉልበትም ሆነ በተወሰኑ የማምረቻ ዘዴዎች ላይ የግል ባለቤት እንደመሆኑ መጠን የራሱን የግል ዓላማዎች እና እቅዶች መሰረት በማድረግ የበለጠ ትርፍ ሊያስገኝለት (ሊያገኝበት) የሚችለውን ሥራ ማፈላለግ ይችላል::»

ሪቻርድ ኤብሊነግ ይህንን ሲሉ አቅጣጫቸው ወደ ነፃ ገበያ እያመራ መሆኑን ልብ ይሏል:: «እያንዳንዳቸው የተለያዩ ዓይነት ንብረቶች ያሏቸውና በተለያዩ መንገዶች ለመተግበር እና ለመጠቀም ነፃ የሆኑ ግለሰቦች ያሉበት ማህበረሰብ ከመንግስት ቁጥጥር (ጫና) ውጭ በሆነ መልኩ በሰዎች መካከል የማምረት፣ የንግድ እና የመደራጀት ግንኙነቶችን የመፍጠር አቅም ያለው መስተጋብርን ያበረክታል::» የሚሉት ሪቻርድ ኤብሊን ይህ ሰላማዊና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የግለሰቦች መስተጋብር የሲቪል ማህበራት (civil society) ንጥረ ነገሮችን እንደሚፈጥር ይገልፃሉ::

ሲቪል ማህበራት በመንግስት ሥልጣን እና በአንድ በነጠላ ግለሰብ መካከል የሚቆሙ አስማሚ (intermediary) ተቋማት ናቸው፤ ለግለሰቡ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና መንፈሳዊ የህይወት ፍላጐቶቹ ድጋፍ እና እርዳታን ያቀርባሉ:: በተጨማሪ የመንግስትን ጉልበት በራሱ የመጋፈጥ እጣፈንታ ለገጠመው ብቻኛ ግለሰብም ጥበቃ እና ጥንካሬ ያበረክታሉ:: እናም ሪቻርድ ኤብሊንግ «ከታሪክ አንፃር አንድ መንግስት በዜጐቹ ጉዳዩች ላይ እጁን መክተቱ እየጨመረ በመጣ ቁጥር እነዚህን ፈቃደኛ የሲቪል ማህበር ተቋማት በተለያዩ መንገዶች ለማስወገድና በራሱ «ቢሮክራቲክ» መዋቅሮች ለመተካት መሞከሩ የሚያስገርም አይሆንም::» በማለት ይገልፃሉ::

ግለሰባዊ ነፃነት ላይ የሚያተኩረው ሊበራሊዝም የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ መሰረት ሆኖ ከተገለፀ የሕግ የበላይነት በአግባቡ ሲተገበርና ሲከበር የግለሰቦች የመፍጠር ብቃት ከመገደብ ይድናል፣ ብሎም የግለሰቦች የፈጠራ ውጤት ለአጠቃላይ ህብረተሰቡ ጥቅም ይውላል:: «እያንዳንዱ ሰው የራሱን እወቀት ለራሱ ዓላማዎች የማዋል ነፃነት አለው፣ ነገር ግን የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ዋና መለያው ግለሰቡ እውቀቱን እና ችሎታዎቹን በህብረተሰቡ ውስጥ የሚገኙትን የሌሎች ሰዎችን ፍላጐቶች በሚያሟላ መንገድ ተግባራዊ ማድረጉ የግድ መሆኑ ላይ ነው::» ይላሉ ጸሀፊው::

ማንም ሰው ቢሆን ከተወሰኑት በስተቀር ሁሉንም ዓላማዎቹን በራሱ ጉልበት እና በውስን ሀብቱ ማሳካት ስለማይችል በህብረተሰቡ ውስጥ ከሌሎች ጋር የመለዋወጥ ግንኙነቶችን ይጀምራል:: በሌላ አገላለጽ ነፃ ገበያን ይፈጥራል:: የሊበራሊዝም ፍልስፍና ይህ እንዲሆን መሰረት ሆኖ ሲገኝ፣ ግለሰቦች በነፃነት ስም የሌሎችን መብት እንዳይጋፉ በተፈጥሯዊ «መቻቻል» ይወሰናሉ፤ እንዲሁም መንግስት በዜጐች መሰረታዊ ነፃነቶች ላይ እጁን እዳያስገባ የሕግ የበላይነት የተባለው መርህ ገድቦ ይይዘዋል::

የሕግ የበላይነት ተግባራዊ ሆኖ ከሰላም አልፎ ልማት አምጪ እንዲሆን ህብረተሰቡ የበላይ ሊያደርው የሚገባ ፍትሃዊ ሕግ፣ እንዲሁም ፍትሃዊውን ሕግ ተከትሎ የሚሰራ ህዝብና መንግስት መገኘታቸው የግድ ነው:: ከሁሉም በላይ ግን የህዝባዊ እና ግለሰባዊ ቅንነት ማስፈለጉ ጥያቄ አያሻውም::

## ቃለ-መጠይቅ

# «[ቃሊቲን] ለእኔ እንዲስማማ አድርጌ ተጠቅሜበት ወጥቻለሁ::»

**ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ)**

ሰው በመግጨትና እርዳታ ሳያደርግ በማምለጥ ተከሶ፣ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት «ጥፋተኛ ነህ» ተብሎ፣ የ6 ዓመትና የ18 ሺህ ብር ቅጣት ተጣለበት:: ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይግባኝ ጠየቀና የእስር ጊዜው ወደ 2 ዓመት፣ የገንዘብ ቅጣቱ ወደ 11 ሺህ ብር ዝቅ አለለት:: ሆኖም፣ ጉዳዩ በዚህ አልተጠናቀቀም - ወደ ሰበር ሰሚ ችሎት ሄደ:: ሰበር ሰሚ ችሎቱም ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ዝቅ ያደረገውን የእስር ውሳኔ አፀና:: የገንዘብ ቅጣቱን፣ «ጠ/ፍ/ቤት የገንዘብ ቅነሳ ያደረገበት አጥጋቢ ምክንያት አልቀረበም::» በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤቱን ውሳኔ አፀና፤ በዚህም፣ ከዓመት በላይ የተመላለሰበት የፍ/ቤት ጉዳይ የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ አገኘና ሐምሌ 9/2001 ተቋጨ:: መቋጨቱም በቤተሰቡና በአድናቂዎቹ ሳይ አዲስ ተስፋ ፈነጠቀ - «ማረሚያ ቤት የአመክሮ ጊዜ ከሰጠው ከ28 ቀናት በኋላ ይለቀቃል» የሚል:: ጉጉቱም ወደ እውነትነት ተቀየረ:: «ሐሙስ የቀን ቅዱስ» ቢል ለሱ በትክክል ይሰራል:: የመጨረሻ ውሳኔ ባገኘበት ሐሙስ (ሐምሌ 9/2001)፣ በችሎት ከአድናቂዎቹ ጋር ደስታን የተጋራው ይህ የጥበብ ሰው፣ ቀሪ አራት ሐሙሶችን በቃሊቲ ማረሚያ ቤት በማሳለፍ የማረሚያ ቤት ወዳጆችን ተሰናብቶ፣ ሐሙስ (ነሐሴ 7) ማምሻውን ከ484 ቀናት የቃሊቲ ቆይታ በኋላ በገደብ የመንቀሳቀስ ጉዞን ተሰናበተ - የግጥምና የዜማ ደራሲ አርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ):: ተቃራኒ ክስተቶችን እያስተናገደች ፈጣን ጉዞዋን የምትቀጥለው ዓለም ሳይ ሲኖሩ ሁሌም የተደላደለ ነገር እንደማይገጥም መገንዘብ ሳልከበደው ቴዎድሮስ ካሳሁን፣ የእስር ጊዜ ከባድ መሆኑን ባይዘነጋም አሳማረረም:: «በአስቸጋሪ ነገሮች ውስጥ ማለፍ ጠንካራ ሰው ያደርግሃል» ሲል ራሱን ያበረታል::

ዛሬ ቴዲና ወዳጆቹ ጋር ለውጥ አለ:: ሳምንት ጠብቀው፣ በጊዜና ቦታ ተገድበው ከመከለያ አጥር «ወዲያና ወዲህ» ሆነው የሚያወጉት ወግ፣ አሁን በጠረጴዛ ዙሪያ አሲያም ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ ለማድረግ የሚያግዳቸው የለም:: የጥየቃ ሰዓት አለቀ አላለቀ እያሉ ሰዓታቸውን ቶሎ ቶሎ እየደጋገሙ መመልከትም አይጠበቅባቸውም:: ገደብ የሌለበት ነፃነት፣ ደስታ እና ፍቅር መጋራት ጀምረዋል::

ድምፃዊው፣ እንግዶቹን በወሳጅ እናቱ መኖሪያ ቤት ፍጹም ኢትዮጵያዊነትን በተላበሰ ጨዋነት ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ ያስተናግዳል፣ ይጋብዛል፡፡ «ብሉ ጠጡ» ከአፉ አልተለየውም፡፡ *ከአውራምባ ታይምስ* **ዳዊት** ከበደ እና **አቤል ዓለማየሁ** «እንኳን ደስ አለህ! እንኳን ለቤትህ አበቃህ!» የሚል መልካም ምኞታቸውን በማስቀደም ከድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ጋር ተከታዩን ቃለምልልስ አድርገዋል፡፡

**ማረሚያ ቤት ውስጥ በሕይወትህ አጋጥመውህ የማያወቁ ነገሮች ትመለከታለህ፡፡ ቃሊቲ በመግባትህ ያገኘኸው የተለየ ነገር ምንድን ነው?**

*ብዙ ጊዜ አስቸጋሪ ነገሮችን ማለፍ ጠንካራ ሰው ያደርጋል፡፡ ሕይወት ሁሌም የተመቸ መንገድ የላትም፡፡ በአጋጣሚም የተሞላች ናት፡፡ በእጣ-ፈንታም ትመራለች፡፡ ዋናው ነገር ሁሉንም እንደ አመጣጡ በመሸኘት በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ አልፎ ጤንነትን ይዞ መዝለቅ ነው፡፡ ቃሊቲ ብዙ አይነት ሰው ይኖራል፡፡ ከብዙ ዓይነት ሰው ጋር ትገናኛለህ፡፡ ጠንካራ ሰው ለመሆን አስቸጋሪ ነገሮችን ማለፍ ባይመረጥም፣ ሕይወት ላይ ያለ ነገር ነው፡፡ ይሄን ተቀብሎ በጽናት ማለፍ ጥሩ ነው፡፡*

**ውጪ ብሆን ኖሮ አላያቸውም ያልካቸው፣ ቃሊቲ የፈጠረልኝ መልካም አጋጣሚዎች ናቸው የምትላቸው የሉም?**

*የተለየ ነገር ሊኖር ይችላል፡፡ አሁን በዚህ ሰዓት (በቃለ-ምልልሱ ወቅት) ላይመጣልኝ ይችላል፡፡ ምናልባት ትዝ የሚለኝ ከጨረስን በኋላ ይሆናል (እየሳቀ)፡፡ እኔ ከባህሪዬ ለጥሩም ሆነ ለመጥፎ ነገር ብዙ መደነቅ አልወድም፡፡ ብዙ መደሰትም ሆነ ማዘን ጥሩ አይደለም፡፡*

**ማረሚያ ቤት ከመግባትህ በፊት ሰው ለመጠየቅ ሄደህ ሳታወቅ አይቀርምና ከደጅ ውስጡን በአይነ-ህሊናህ የምትስለው ነገር ይኖራል፡፡ ስትገባስ እንዴት አገኘኸው?**

*በጣም ይገርምሀል . . . መጀመሪያ የገባሁበት ቦታ ዞን 6 ይባላል፡፡ እዚያ ያሉ ልጆች በጣም ነው የተንከባከቡኝ፤ በዚህ አጋጣሚ ሞቅ አድርጌም አመሰግናቸዋለሁ፡፡ ቀጥሎ ትንሽ ጊዜ (ከ2 ወር በላይ) ብቻዬን ነበርኩ፡፡ ትንሽ ከባዷ ጊዜ እሷ ነበረች፡፡ ረዥም ጊዜ የነበርኩት ዞን 5 ውስጥ ነው፡፡ ቆይታዬም ጥሩ ነበር፡፡ ከሰዎች ጋር ጥሩ መግባባት ነበረኝ፡፡ እንዳልኳችሁ እኔ የሆነው ነገር ሲመጣ ዝም ብዬ መጓዝ ነው፡፡ ኧ . . . ጥሩ ነው፡፡*

**የአንተ ጉዳይ በሚታይበት ችሎት የነበረው የታዳሚ ቁጥር ብዛት አስገራሚ ነበር:: የሰራነው ጥናት ባይኖርም በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶ የሚታወቅ አይመስለንም:: በሕግ ጥበቃ ስር ሆነህ የሰዉን ነገር ስትመለከት ምን ይሰማህ ነበር?**

ሰዉ በጣም ያሳዝነኝ ነበር:: በጣም እጨነቅ የነበረውም ለሰዉ ነው:: ከዚህ በፊትም ገልጬአለ ሰዉ ብዙ «እዳ» አስቀምጦብኛል:: በየችሎቱ ያልቀሩ፣ እስክፊታ ድረስ ማረሚያ ቤት የተመላለሱ ብዙ ሰዎች አሉ:: ሁሉንም በጣም ማመስገን እፈልጋለሁ:: ሲያለቅሱ ሳይ ያሳዝነኛል:: እኔ ደግሞ ማልቀስ አልወድም (እየሳቀ):: ሰዉን ሳይ ግን እንባ ይተናነቀኝ ነበር:: አይዟችሁ ሁሉም በጥሩ ሁኔታ አልፏል እላቸዋለሁ::

**በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በነበረ አንድ ችሎት ሳይ የጠጣህበትን የውሃ እቃ ተሯሩጣ ሄዳ በማግኘቷ በጣም በደስታ አምላኳን ያመሰገነች ሴት ተመልክተናል:: (በወቅቱ ችሎቱን ለቆ እየወጣ የነበረ ቢሆንም ክስተቱን ቴዲ አስታወሶታል::) ከአረብ አገር እግሯን ታማ የመጣች ሴት አንተን ለመጠየቅ ከጉዳቷ ሳታገግም እያነከሰች ቃሊቲ መገኘቷን እናውቃለን:: ከክ/ሀገር ድረስ ያንተን ችሎት ለመታደም የሚመጡ ወጣቶች ነበሩ:: «ፋይናል» ፈተና ጥሳ ከችሎት የታደመች ሴትን አስታውሳለሁ:: ይህ ፍቅር ምንድነው? ምንስ ይሰማሀል?**

እኔ እንዲህ ነው ብዬ የምናገርበት ቃላት የለኝም:: ብዙዎች ስለ እኔ ያለቅሱ ነበር:: ከእኔ በላይ የተጐዱ እነሱ ናቸው ብዬ ብናገር ድፍረትም ውሸትም አይደለም:: ላያስችል አይሰጥም:: እስር ቀላል ነገር አይደለም:: ከባድ መሆኑንም ከመናገርም በላይ አውቀዋለሁ:: ግን እነሱ (አድናቂዎቹ) ደግሞ፣ ምን ልበልህ . . . በጣም በጣም . . . ብቻ ቃላት የለኝም:: (ለመግለጽ በሚከብድ ስሜት ውስጥ ሆኖ፤)

**ይህን ሁሉ ስትመለከት፣ «ቴዲ እንዲህ ሲኮንበት የሚገባ ሰው ነውን?» ብለህ ራስህን ጠይቀህ ታውቃለህ?**

የማስበው አይገባኝም ብዬ ነው:: ነፍሱን ይማረውና ጥላሁን ከመሞቱ በፊት ሊዘፍነው የነበረና በሙያ ጓደኞቹ የተዘፈነው «በስውር ጥበብህ ሳይገባኝ ያከበርከኝ» የሚለው ዘፈን በጣም ይማርከኛል:: እኔ እግዚአብሔር ሳይገባኝ አክብሮኛል::

**ማረሚያ ቤት ሆነህ «አይን አፋር ነኝ» እና ያለ ሙዚቃ መሣሪያ የተጫወትከው «ሳምባዲና» የሚሉት ሁለት ዜማዎች ተለቀው ነበር:: ዜማዎቹ ማን እጅ ሳይ ነበሩ? በምን ሁኔታስ የወጡ ይመስልሀል?**

ከእኔ እውቅና ውጪ ናቸው:: በማን እጅ እንደነበሩ አላውቅም:: ከዚህ በፊትም ከ4 የላነሱ ዘፈኖቼ ከእኔ እውቅና ውጪ ወጥተዋል:: ቤቴ በኪቦርድ የተጫወትኳቸው

ሳምፕል ዜማዎች ናቸው:: መኪና ውስጥ ብዙ ጊዜ እይዛቸው ነበር:: መኪናህን ደግሞ ለአጣቢ ትሰጣለህ:: ምናልባት . . . ብዙ አጣቢዎች ስላሉ እንግዲህ ሁሉንም ስላልተናገርኩ እንደማይቀየሙኝ እርግጠኛ ነኝ:: (እየሳቀ):: ለክፋትም የሆነ ነገር አይመስለኝም:: አንድ ሰው ለክፋት (ለጥቅም) ቢያስበው ኖሮ ወስዶ ሊጠቀምበት ይችል ነበር:: ተደብቀህ የምትሰማው ነገር ሳይታሰብ አድማጭ ጋር የደረሰበት ሁኔታ የተፈጠረ ይመስለኛል::

**በማረሚያ ቤት ቆይታህ ኦርጋን ገብቶልሀል የሚባል ወሬ ነበር?**

አይ ኦርጋን አልገባልኝም:: በነገራችን ላይ፣ ከማረሚያ ቤቱ ሥራ አስኪያጅ እስከ በታች ሰራተኞች ድረስ ጥሩ ሊረዱኝ ሞክረዋል:: የፍርድ ውሳኔ ሲሰሙ የሚያለቅሱ ፖሊሶች ነበሩ:: (ይህን እኛም ለመታዘብ ችለናል::) ዲቪዲ እንዲገባልኝ ጠይቄ ገብቶልኛል:: መጽሐፍቶች ይገቡልኝ ነበር:: እኔም ደስ ያለኝን እጽፍ ነበር:: ጊዜው ያለፈው በዚህ ሁኔታ ነው::

**የፃፍካቸውን ጽሁፎች በሙሉ ስማውጣት ችስሀል?**

አዎ አሉኝ:: ስወጣ ሁሉንም ይዣቸው ወጥቻለሁ::

**ኦርጋን አልገባልኝም አልክ እንጂ እኔ የሰማሁት «ሪከርድ» ማድረግ እንደቻልክ ሁሉ ነበር:: ትክክል ነኝ?**

አይ በፍፁም ተሳስተሀል:: የመቅጃ መሳሪያዎች አይገቡም:: ዜማ ሲመጣልኝ እንኳን የምቀዳበት ስለማጣ . . . እንደውም አንድ ጊዜ የመጣልኝ ዜማ እንዳይጠፋብኝ ከአንድ ሰዓት በላይ መታጠቢያ ቤት ቆሜ እደጋግመው ነበር:: መጨረሻ ላይ ግን እንደምንም ያዝኩት:: ከዚያ በኋላ ግን አልደፈርኩም ተውኩት:: ምክንያቱም አንድን ዜማ አንድ ሰዓት ሙሉ ለመያዝ መሞከር ከባድ ነው፤ ለመቅዳት አይመችምና::

**ያነበብካቸው ምን አይነት መጽሐፍትን ነበር?**

የታሪክና በሰዎች ግለ-ታሪክ ላይ የተፃፉ መጽሐፍቶችን ማንበብ እወዳለሁ:: የፍልስፍና መጽሐፍቶችንም እወዳለሁ:: ልብ ወለድ ካነበብኩ ቆይቼ የነበረ ቢሆንም ቃሊቲ ግን ለማንበብ ችያለሁ:: የወጣሁት እንደ ሞባይል [የእውቀት ኃይሌን] ቻርድ አድርጌ ነው::

**የመጽሐፎቹን ርዕስ ልትነግረን ትችላለህ?**

ምንም ችግር የለም:: «የ20ኛው ክ/ዘመን ኢትዮጵያ»ን ሁለት ጊዜ አንብቤዋለሁ:: የብላቴን ጌታ ህሩይን መጽሐፍ አንብቤያለሁ:: «The Secret»ን ጨምሮ ብዙ መጽሐፍትን መጥቀስ ይቻላል::

**ለ32ኛ ዓመት ሕይወትህ ንገረን ብንልህ እስር ቤት ውስጥ ጀምረህ ትጨርሰዋለህ:: በሕይወትህ መጥፎው የምትለው ዓመት ይህ ነው?**

ከባድ ጊዜ ሊሆን ይችላል:: መጥፎ ጊዜ ለማለት ግን አልደፍርም:: ነገሮችን የሚሰራቸው ከውስጥ የምታመነጨው ኃይል ነው:: ጥሩ ካሰብክ፣ ነገሮች ጥሩ እንዲሆኑ ካደረክ፣ ጥሩ ከተናገርክ፣ ጥሩ ነገርን የምትጠራው አንተ ነህ:: ቦታውን [ቃሊቲን] ለእኔ እንዲስማማ አድርጌ ተጠቅሜበት ወጥቻለሁ:: አስቸጋሪ ነገሮች ጠቅመውህ እንደሚያልፉ እምነት ካለህ እግዚአብሔር ለበጐ አድርጐ ይቀይርልሀል::

**ከእስር ቤት ስትወጣ ይቅርታ ጠይቀሀል?**

ይቅርታ የሚያስጠይቀኝ ነገር የለም፣ ይቅርታም አልጠየኩም:: በአመክሮ የሚፈታ ማንኛውም ታራሚ ከማረሚያ ቤት ሲወጣ ሊያሟላ የሚገባው መስፈርት አለ:: የምትወጣው የሕግ የበላይነትን፣ የወንጀል አስከፊነትን ተምሬያለሁ ብለህ ነው:: ያን አድርጌ ወጥቻለሁ:: እኔ ሰው አልገጨሁም፣ አልገደልኩም፤ ነገር ግን፣ የፍ/ቤት ውሳኔን አከብራለሁ:: ውሳኔውን አክብሬም የእስር ጊዜዬን ጨርሼ ወጥቻለሁ:: ወደ ይቅርታ የሚወስደን ምንም ምክንያት የለም::

## ***Motivation***

# መሳሳብ

**በባንቺወሰን ወልደየሱስ**

**«ዓለም ትልቅ መስታወት ነው:: የሚያንፀባርቅልህ አንተ የሆንከውን ነው:: በውስጥህ ፍቅር ያለህ፣ ተግባቢና ረጂ ከሆንክ ዓለም ላንተ ፍቅር ነው፤ ጓደኛንና አንተን የሚረዳ ይሆናል:: ዓለም አንተ እንደሆንከው ነው የሚሆነው::»**

**ቶማስ ድሬር**

እስኪ ማነው ከፊቱ ላይ ፈገግታ የማይለየው ሰው ጋር ሆኖ የሚቆጣ? ማነው ከጠንካራ ሰራተኛ ጋር ሆኖ እሱ ግን ጉበዝ ያልሆነ? ማነው እጅግ በጣም ከሚግባባ ሰው ጋር ሆኖ እሱ ግን በትንሹም ቢሆን መግባባት ያልቻለ? ማን አለ ፍቅር ለሁሉም እየሰጠ

እሱ ግን በምላሹ ፍቅር ያላገኘ? ማነው ለሌላው መልካም ነገርን ሰጥቶ ምላሽ ያላገኘ? ማን አለ እሱ የሆነውን አንፀባርቆ ካሳየው ነገር የሚመሳሰል በምላሹ ያላገኘ?

**«ደስተኛ ሰዎች አጠገብህ ሲሆኑ ራስህን ዘና ብሎ ታገኘዋለህ፡፡ ታዲያ ለምን አንተስ ያንን የደስታ ስሜት ሌሎች ላይ ለመፍጠር ከልብህ አትጥርም? የጦርነቱን ግማሽ ያህል ማሸነፍ የሚቻለው ራስህ ለራስህ መቼም ቢሆን ደብዛዛ ነገር እንዲናገር ካልፈቀድክለት ነው፡፡»**

**ሊዲያ ሜ.ቻይልድ**

ምንም እንኳን አንድ ሰው ደስተኛነቱን፣ ፍቅሩንና አሳቢነቱን ለሌላው በሀሳብና በተግባር እያንጸባረቀ በምላሹ ተመሳሳይ ባህሪያትን ሁልጊዜ በእርግጠኝነት ያገኛል ማለት ባይቻልም የማግኘቱ ዕድል ግን እጅግ በጣም ሰፊ ነው፡፡ ያ ሰው ይህን ዕድል ባያገኝ ያላገኘው እንዳያገኝ በአሳሪ ሕግ ስለታገደ አይደለም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ እንደሕግ ወይም እንደ አንድ እንደሚሆን ነገር መውሰድ የምንችለው፣ አንድ ሰው ከአካባቢው (ከጓደኞቹ፣ ከቤተሰቡ፣ ከስራ ባልደረቦቹ ወዘተ) ለማንኛውም ነገር የሚያገኘው ምላሽ እሱ ካሳየው ባህሪ ጋር አቻ ወይም ተቀራራቢ የሆነ ነው - ልክ በመስታወት ውስጥ የሚመለከተው የራሱን መልክ እንደሆነው ሁሉ ማለት ነው፡፡ እሱ ደግ በሆነ ቁጥር በዙሪያው ደግ የሆኑ ሰዎችን የማግኘቱ ዕድል ከፍተኛ ነው፡፡ ይሄ ዕድልም ብቻ ሳይሆን በተለይ ያ ሰው አልፎ አልፎ ሳይሆን ሁልጊዜ ደግ ከሆነ፣ ለሰዎች ጥሩ ካደረጉ ምላሹ በእርግጠኝነት ጥሩ እንደሚሆን የሚያውቁ በርካታ ተመሳሳይ መልካም ባህሪ የሚያመነጩ ሰዎችን ያፈራል፡፡ ምክንያቱም ሁልጊዜ ጥሩ ፊት ለሚያሳየን ሰው እንዴት እኛ ሁልጊዜ ሌላ እንሆናለን? ይሄ ከባድ ሥራ አይሆንብንም? እንደዚህ ዓይነት ሥራ ከከባድ ሥራነቱም አልፎ ትርጉም የሌለው ስራ ነው፡፡ ይህም የሚሆነው እኛ ሌላ ፊት ብናሳይም የዛ ሰው መልካም ፊት ግን ስለማይቀየር ነው፡፡ በተጨማሪም፣ ሌሎች ተመሳሳይ ባህር የሚያንፀባርቁ ሰዎችን ያስባል፡፡ እናም፣ ራስን ከዛ ከምናየው ባህሪ ለመለየትና ያን ባህሪ እኛ እንዳናንፀባርቅ ለማድረግ ከባድና የበለጠ አስቸጋሪ እየሆነ ይሄዳል፡፡ ለዛም ነው አንድ ሰው ሳቂታ በሆነ ቁጥር ብዙ ፈገግ የሚሉ ሰዎች አጠገቡ የሚኖሩት፤ ብዙ ፍቅር በሰጠ ቁጥር በምላሹ ብዙ ፍቅር የሚያገኘው፤ ሁሌ ለሌሎች አሳቢ በሆነ ቁጥር ብዙ ለእሱ የሚያስቡ ሰዎች የሚኖሩት፤ ሌሎችን ባከበረ ቁጥር ያንን ሰው የሚያከብሩ ሰዎች ብዙ የሚሆኑት፤ ለሌላው ባሰበ ቁጥር ለእሱም የሚያስብና የሚጨነቅ ሰው ይኖራል፡፡

በአጠቃላ፣ አንድ ሰው ደስተኛ በሆነ ቁጥርና ይህንንም ደስታ ለሌላው ባሳየና ባካፈለ ቁጥር፣ ሌሎች ደስተኞችን እያፈራ ይሄዳል፤ ውጤቱም አመርቂ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም፣ ሰው ደስታ ምን ማለት እንደሆነ ብቻውን ከሚያውቀውና ከሚያጣጥመው ይልቅ ከሌሎች ጋር ቢጋራውና ቢካፈለው ደስታን የሚያገኘው እንደ ሰዎቹ ብዛት በእኩሌታ ተከፋፍሎና አንሶ ሳይሆን መጀመሪያ ከነበረው ይዘት በልጦ ብዙ፣ እጅግ ብዙ ሆኖ ነው፡፡ ማንኛውንም ጥሩ ነገር አንድ ሰው ብቻውን ከሚያገኘው ከሰዎች ጋር

ቢካፈለው ያ ጥሩ ነገር እጥፍ ድርብ ይሆናል፡፡ ለዛም ነው «ደስታን ሲጋሩት እጥፍ ይሆናል» የሚባለው፡፡

ይሄ የመሳሳብ ሂደት ጥሩ ባልሆነውም ጐን ይሰራል፡፡ ይህም ማለት፣ ለምሳሌ ሁሌ ከሚቆጣ ሰው ጋር ስንሆን እኛ የማንቆጣ ለመሆን ከፈለግን በጣም አስቸጋሪ ነው የሚሆንብን፡፡ በጊዜ ብዛት እኛም የምንቆጣ እንሆናለን ወይም ከዛ ሰው ጋር አብረን መቆየት ያቅተናል፡፡ ተቃራኒ የሆኑ ባህርያት ምናልባት አንድ የሚያስተሳስራቸው ነገር ከሌለ በስተቀር አንድ ላይ ተዋደውና ተፈላልገው የሚቆዩበት ሁኔታ የለም፡፡ ልክ ጥሩ ፊት ሲያሳየን ለነበረ ሰው ተቃራኒውን ፊት ማሳየት እንደተቸገርነው ሁሉ ጥሩ ፊት ከማያሳየን ሰው ፊት እኛ ሁሌ ጥሩ ፊት ለማሳየት እንቸገራለን፡፡ ጊዜው ሌላ ፊት እያሳየ ያለውን ወደእሱ ይስበዋል ወይም ደግሞ ጥሩ ፊት የሚያሳየው ሰው ጥሩ ፊት እያሳየ ያለውን ወደ እሱ ይስበዋል፡፡ እነዚህ ሁለት አማራጮች ካልሆኑ ደግሞ ሁለቱ ሰዎች አንድ ላይ ተግባብተው ለረጅም ጊዜ በምንም ሁኔታ አብረው መቆየት አይችሉም፡፡

**«አንድ ሰው ደግና አሳቢ እየሆነ በሄደ ቁጥር የበለጠ ደግነትን ሌሎች ላይ እያገኘ ይሄዳል»**

**ሊዮ ቶልስቶይ**